የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
የኘሮግራም በጀት አፈጻጸም ውጤታማነትን
በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ማውጫ

ማጠቃለያ EXCUTIVE SUMMERY

ክፍል አንድ......1

መግቢያ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር...... 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት 4

የፋይናንስ ምንጭ...... 5

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሥራ ሂደት መግለጫ 5

የኦዲቱ አላማ 6

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች...... 6

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት 7

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 7

ክፍል ሁለት......8

የኦዲት ግኝቶች 8

ሀ. የባለበጀት መ/ቤቶች ያዘጋጁት የፕሮግራም በጀት በተያዘለት ጊዜና ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተልና ለመገምገም የተዘረጋው ሥርዓት ጠንካራ መሆኑን እንዲሁም የፕሮግራም በጀት በመተግበር የሚጠበቀው ውጤት የተገኘ መሆኑን በተመለከተ፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለበጀት መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት መርሐ ግብርና የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን በማንዋሉ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲያቀርቡ ማድረጉን በተመለከተ፣ 8

የፕሮግራም በጀትን ተግባራዊ ያደረጉ ባለበጀት መ/ቤቶች በመርሃ ግብራቸው መሠረት ሥራ አፈጻጸማቸው ላይ ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤ 12

ሚኒስቴር መቤቱ መ/ቤቶችን የመስክ ጉብኝት እና ቅኝት ለማድረግ መርሃ ግብር በማዘጋጀት በመርሃግብሩ መሰረት መከታተሉን በተመለከተ፤ 14

የፕሮግሞች ውጤት ከግብ ስኬት አንጻር መገምገሙን በተመለከተ፤ 21

ለ. የፕሮግራም በጀት አላማዎችን ለማስፈጸም የተዘረጋው ሥርአት፣ ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

መ/ቤቶቹ ፕሮግራም በጀትን ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት መኖራቸውንና የፕሮግራም በጀት እና ውጤት ተኮር ዕቅድ ለማቀናጀት የተሰሩ ሥራዎችንበተመለከተ 23

በመ/ቤቶች ከፕሮግራም ወደ ፕሮግራም የሚደረግ የበጀት ዝውውር
አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያን መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤ 26
መ/ቤቶች ሥርዓት ያታን በፕሮግራሞቻቸውና
በፕሮጀክቶቻቸው ማካተታቸውን በተመለከተ፤ 33
ሚኒስትር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀትን በሁሉም የመንግሥት
መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም.ጀምሮ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡.. 34

ሐ. ሚኒስትር መ/ቤቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት እና ድጋፍ እንዲሁም ጠንካራ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ትስስር የፈጠረ መሆኑን በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች
ተከታታይ ሥልጠናና ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፤ 38
ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮግራም በጀት ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠሩን፣
በዕቅድ እና በበጀት ዝግጅት እንዲሁም በበጀት አስተዳደር ያጋጠሙ
ችግሮችን ለመፍታት ከባለበጀት መ/ቤች ጋር ውይይት ማካሄዱን በተመለከተ፤ 39

ክፍል ሦስት 43

መደመደሚያ

ክፍል አራት 47

የማሻሻያ ሐሳቦች

አባሪ 1 50

በናሙና በታዩ መ/ቤቶች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ የማይጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

አባሪ 2 55

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

ዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (Executive Summery)

1. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ሀብትን ከውጤት ጋር ለማስተሳሰር እየተደረገ ያለውን ጥረት ለማገዝ እና የመሠረተ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥን ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን እንዲሁም ለፕሮግራሞችና ለካፒታል ፕሮጀክቶች የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተል የተዘረጋውን የፕሮግራም በጀት ሥርዓት አፈጻጸም በመገምገም በአሠራር ላይ ክፍተቶች ከታዩ እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ ለመስጠት እና ተጠያቂነትን በማስፈን ማገዝ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸምን አስመልክቶ ቅኝትና የመስክ ጉብኝት ለማድረግ በ2008 ዓ.ም. ብቻ ዝርዝር መርሐ ግብር ያዘጋጀ ሲሆን በ2007 ከ155 መ/ቤቶች ሦስት /9%/ መ/ቤቶች ላይ ብቻ እንዲሁም በ2008 ዓ.ም. ከ165 ባለበጀት መ/ቤቶች በ5ቱ ላይ ብቻ 23 ፕሮጀክቶች ብቻ ለማየት መርሐ ግብር ተይዞ በሦስት ባለበጀት መ/ቤቶች በጠቅላላው 5 ፕሮጀክቶች/3%/ ላይ ብቻ የመስክ ጉብኝት የተደረገ ሲሆን በሌሎች መ/ቤቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የመስክ ጉብኝት አለመደረጉ፣

3. መ/ቤቶች መርሃ ግብር አዘጋጅተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረባቸውና በመርሃ ግብርቸው መሰረት መፈጸማቸውን በተመለከተ በጊዜ መርሃ ግብራቸውንም ሆነ የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን የማያቀርቡ መ/ቤቶች መኖራቸው፣

4. የተሟላ ሪፖርት የማያቀርቡ ማለትም በፋይናንሻል አፈጻጸም ላይ ብቻ የተመሰረተ/የፊዚካል እና የፕሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርት የማያቀርቡ/ መ/ቤቶች መኖራቸው፣

5. የማስፈጸም አቅምን ያላገናዘበ መርሃ ግብር የሚያቀርቡ፣ ከሚያቀርቡት መርሃ ግብር ጋር ያልተጣጣመ ሪፖርት የሚያቀርቡ መ/ቤቶች መኖራቸው፣

6. መ/ቤቶች ከመርሐ ግብር አንጻር አፈጻጸማቸው በተከታታይ በየሩብ ዓመቱ የማይገመገሙ መ/ቤቶች መኖራቸውና አፈጻጸማቸው በየሩብ ዓመቱ የሚገመገሙ መ/ቤቶችም ባለው ልዩነት ላይ በቃል አልፎ አልፎ ግብረ መልስ የሚሰጣቸው ቢሆንም ተከታታይነት ባለው መልኩ በዝርዝርና በጥልቀት በጽሑፍ ግብረ መልስ

የማይሰጣቸው መሆኑና ከተጠያቂነት አንጻርም የግምገማ ሪፖርቱ ለየትኛውም አካል የማይቀርብ መሆኑ፣

7. በመሆኑም በፌዴራል ደረጃ መንግስት ከፍተኛ በጀት የሚመድበው በካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በ8 መ/ቤቶች/የዲላ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲዎች፣ የውሃ፣ የመስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እና ማረሚያ ቤቶች/ በመርሐ ግብር በተያዘላቸው በጀት የማያልቁ ፕሮጀክቶች/የመስኖ ግድቦ ግንባታ/ መኖራቸው እንዲሁም በአዳማና በዲላ ዩኒቨርስቲዎችና በመንገዶች ባለሥልጣን በሥራ ተቋራጮች በውላቸው መሰረት ባለመስራታቸው ምክንያት የሚቋረጡ ኘሮጀክቶች መኖራቸው እና በናሙና በታዩት በሁሉም መ/ቤቶች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ የማይጠናቀቁ ኘሮጀክቶች መኖራቸው፣

8. በየዓመቱም ሆነ በየሦስት ዓመቱ /ከ2004-2006 በጀት ዓመት/ የመ/ቤቶች ኘሮግራሞች ከግብ ስኬትና ከመጀመሪያው ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንጻር ያመጡት ውጤት አለመገምገማቸው፣

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኘሮግራም በጀትን ለማስተግበር የሚያስችል የሰው ኃይል የሌለው ማለትም በመዋቅር 47 የተፈቀደለት ቢሆንም ያለው 20 /42%/ የሰው ኃይል ብቻ መሆኑና ከባለበጀት መ/ቤቶች ብዛት /165/ መ/ቤቶች/ አንጻር ሲታይ ወጥና ቀጣይነት ያለው የመስክ ጉብኝትና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የተለየ የክትትልና ግምገማ ክፍል አለመኖሩ፣

10. የኘሮግራም በጀትና የውጤት ተኮር/BSC/ በአገር አቀፍ ደረጃ አለመቀናጀቱና ባለበጀት መ/ቤቶች ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው የተለያዩ አካላት ከዕቅድ ጀምሮ እስከ አፈጻጸም የተለያየ ሪፖርት የሚያዘጋጁ መሆኑ በግምገማ ሥራ ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ መሆኑና ለሪፖርቱ መዘግየትና ጥራት ማነስ አንዱ ምክንያት መሆኑ፣

11. በኘሮግራም በጀት መሰረት የተፈቀደው በጀት ለኘሮግራሙ ማስፈጸሚያ ሳይውል የበጀት ዝውውር በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ፣ የበጀት ዓመቱ ማለቂያ አንድ ወር ሲቀረው እና ዓመቱን ሙሉ የበጀት ዝውውር የሚያደርጉ መ/ቤቶች መኖራቸው፣ የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 10/3-ለ መሰረት ዝውውሩ ለምን እንደተደረገ በቂ ማብራሪያና ደጋፊ ማስረጃዎች

የማይያያዘና በውጤቶች፣ በዋና ዋና መደበኛ ተግባራት ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ የማይገመገም መሆኑ፣

12. በሁሉም ክልል ፕሮግራም በጀት እየተሰራበት አለመሆኑ፣ በፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች በማንዋሉ መሰረት እየተተገበረ አለመሆኑና የፕሮግራም በጀት ትግበራ አሁን የደረሰበትንና ከተጀመረበት ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ በፌዴራል ደረጃ ያመጣው ውጤት /ለውጥ/ አለመገምገሙ፣

13. ሥርዓተ ጾታን በተመለከተ በማንዋሉ መሰረት በናሙና በታዩ መ/ቤቶች ከውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር በስተቀር በሌሎቹ ተቋማት በበጀት፣ ዕቅዶቻቸው እና በአፈጻጸም ሪፖርቶቻቸው ላይ የሴቶች ተጠቃሚነትን የማያሳዩ መሆኑ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ትኩረት ሰጥቶ ከሥርዓተ ጾታ አንጻር የመ/ቤቶች ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶች ዕቅድ ሆነ አፈጻጸማቸው የማይገመገም መሆኑ፣

14. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለባለበጀት መ/ቤቶች ከ2006-2008 ዓ.ም. በየዓመቱ ለ3 ቀን የሚሰጠው ስልጠና ፕሮግራም በጀትን ለመተግበር በቂ አለመሆኑና የስልጠና አሰጣጡም በገለጻ /orientation/ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ፣ በሚሰጠው ስልጠናም የፕሮግራሙ ባለቤት ለሆኑ የሥራ አመራሮች ስልጠናውን እንዲያገኙ አለመደረጉ፣

15. በበጀት ዝግጅት እንዲሁም በበጀት አስተዳደር ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት የውይይት መድረክ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመዘጋጀቱ፣ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮግራም በጀትን በተመለከተ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ አለመሥራቱ፣

16. በፕሮግራም በጀት አሠራር መሠረት የሚከናወኑ ተግባራት ወጪዎችን ከውጤቶች ጋር አስተሳስሮ መዝግቦ በመያዝ በኩል ሥራውን የሚያሳልጥ በሁሉም መ/ቤት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አለመዘርጋቱ፣

የሚሉ ናቸው፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የፕሮግራም በጀት አሠራር ሥርዓት ዋና ዓላማ ፕሮግራም አደረጃጀትን በመጠቀም ሀብትን ለውጤት መመደብ ነው፡፡ የፕሮግራም አደረጃጀት የአሠራር ሥርዓቱ ቁልፍ የመተንተኛ መሣሪያ ከመሆኑም በላይ የዕቅድና የበጀት ትስስርን የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን የመደበኛና የካፒታል ወጭዎችን ለማቀናጀት ያገለግላል፡፡ ለመሥሪያ ቤቶች በበጀት አስተዳደር ነፃነትን በመስጠት ለውጤቶች ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ያሰፍናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመሠረተ ልማትን በማከናወን፣ አገልግሎቶችን በመስጠትና የተገኙትንም ውጤቶች ለመለካት ያስችላል፡፡

2. በአጠቃላይ የፕሮግራም በጀት፣ በጀትን ከውጤት ጋር የሚያዛምድ የበጀት አሠራር ሥርዓት ሲሆን፣ ውጤትን ለመለካት፣ ተጠያቂነትና ግልጽነትን ለማስፈን፣ ፖሊሲና ስትራቴጂክ መሠረት በማድረግ ዕቅድን ከበጀት ጋር ለማስተሳሰር እና የመደበኛና ካፒታል ወጪዎችን ለማቀናጀት የሚያስችል ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡

3. የፕሮግራም በጀት ከብዙ የበጀት ሥርዓቶች አንዱ ሲሆን፣ ሌሎች የበጀት ሥርዓቶች የሆኑት የዜሮ መሰረት በጀት/Zero Based Budget/፣ የዝርዝር የወጪ አርዕስት በጀት/Line Item Budget/፣ የፐርፎርማንስ በጀት /Performance Budget/ ናቸው፡፡ ለሥርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት /Gender Responsive Budget/ ደግሞ ሥርዓተ ጾታን በበጀት ውስጥ ለማካተት የሚረዳ የሌሎቹ የበጀት ሥርዓቶች አካል ነው፡፡ በሀገራችንም በፌዴራል መንግሥት ደረጃ ወደ ፕሮግራም በጀት ሽግግር ከመደረጉ በፊት ሲሰራበት የነበረው የበጀት ሥርዓት የዝርዝር ወጪ አርዕስት/Line Item/ የበጀት ሥርዓት እንደነበረ የሚታወቅ ነው፡፡

4. የፕሮግራም በጀት እና በዝርዝር የወጪ አርዕስት ላይ የተመሰረተው የበጀት ሥርዓት /Line Item Budgeting/ የሚለዩበት ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ተ.ቁ.	ፕሮግራም በጀት	ዝርዝር የወጪ አርዕስት በጀት
1	በውጤት ላይ ያተኩራል	በግብዓት ላይ ያተኩራል
2	ከመስሪያ ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ እንዲሁም ከስትራቴጂክ ዕቅድ ይነሳል	ተልዕኮና ራዕይ እንዲሁም ስትራቴጂክ ዕቅድን አያሳይም
3	የልማት ዕቅድንና በጀትን ያገናኛል	በጀትን በተናጠል ለብቻው ያያል
4	የመደበኛና ካፒታል ወጪዎችን ያቀናጃል	መደበኛና ካፒታል ወጪዎች ለየብቻቸው ተነጣጥለው ይታያሉ
5	ለመሥሪያ ቤቶች ነፃነትን በመስጠት ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ያሰፍናል	በማዕከል ቁጥጥር ላይ የሚያተኩር ሲሆን ለውጤቶች ተጠያቂነትን አያሰፍንም
6	ለክዋኔ ኦዲት መሠረት ይጥላል	አመልካቾችና ግቦችን ስለማያሳይ የክዋኔ ኦዲትን ለማከናወን አመቺ አይደለም
7	በጀቱ ያስገኘውን ውጤት እና የግብ ስኬት ለመለካት ያስችላል	በጀቱ መፈጸሙን እንጂ ያስገኘውን ውጤት ለመለካት አመቺ አይደለም

5. በመሆኑም በአገራችን በ1980ዎቹ መጨረሻ መንግሥት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምን በመንደፍ እያካሄዳቸው ካሉ የተለያዩ የማሻሻያ ጥናቶች አንዱ የበጀት አሰራር ሥርዓት ማሻሻያ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ዙር በተደረገው የበጀት ማሻሻያ በዝርዝር የወጪ አርዕስት ዙርያ በተደረገው የበጀት ሥርዓት በርካታ የማሻሻያ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በሁለተኛው ዙርም የበጀት ማሻሻያውን በመቀጠል የፕሮግራም በጀት አሰራር ሥርዓትን መዘርጋት ሲሆን የፕሮግራም በጀት አሰራር ሥርዓትን በሥራ ላይ ለማዋል ከ1998-2001 ባሉት ዓመታት በተመረጡ መ/ቤቶች ላይ የሙከራ ትግበራ ተደርጓል፡፡ በ2002 በጀት ዓመትም የፌዴራል መ/ቤቶች ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደላቸውን በጀት መሠረት አድርገው በፕሮግራም በጀት አሠራር ተግባራዊ ልምምድ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት በፌዴራል መንግሥት ደረጃ በ2004 በጀት ሙሉ ትግበራ ተደርጓል፡፡

6. የመጀመሪያው ዙር የፕሮግራም በጀት ዘመን /2004-2006/ በ2006 በጀት ዓመት ተጠናቆ፣ የሁለተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት ዘመን/የ2007-2009/ ደግሞ ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ

7. ለፈጣን፣ ዘላቂና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ብቁና መሪ ተቋም መሆን፣

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 እና 916/2008 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ተሰጥቶታል፡-

- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነትና ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ እንዲሁም የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ ያመነጫል፣ አፈፃፀሙንም በመከታተል ኢኮኖሚውን በተገቢው መንገድ ያስተዳድራል፣ የኢኮኖሚውን አፈፃፀም የሚያሳይ ሪፖርት ያቀርባል፣
- የኢኮኖሚ ትብብርና የፊስካል ፖሊሲዎችን በተለይም ለታክስና ለቀረጥ ሕጎች መሠረት የሚሆኑ ፖሊሲዎችን ያመነጫል በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣
- አገራዊ የልማት ዕቅድ አዘገጃጀትና አፈፃፀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የአገሪቱን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
- የልማት ፕሮጀክቶች የአዘገጃጀትና የአፈፃፀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለፋይናንሲንግ በሚቀርቡ ፕሬጀክቶች ላይ የቅድመ-ትግበራ ግምገማ ያካሂዳል፣
- የፌዴራል መንግሥቱን አጠቃላይ፣ የክፍላተ-ኢኮኖሚ የመድብለ ዘርፎች የልማት ዕቅዶች አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የክልሎችን የልማት አፈፃፀም በጥቅሉ የሚያካትት አገራዊ የልማት ዕቅዶች አፈፃፀም ዓመታዊ ሪፖርት ያዘጋጃል፣
- የማክሮ ኢኮኖሚ እና የፊስካል ፖሊሲዎችን በተለይም ለታክስና ለቀረጥ ሕጎች መሠረት የሚሆኑ ፖሊሲዎችን ያመነጫል፣ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣

- የፌዴራል መንግሥትን የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣
- በፌዴራልና በክልል መንግሥታት ደረጃ የሚዘረጉ የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓቶች የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
- የፌዴራል መንግሥቱን በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያ ይፈፅማል፣ የበጀቱን አፈፃፀም ይገመግማል፣ የፌዴራል መንግሥቱን የግዥና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን የቆጣጠራል፣
- የውጭ ዕርዳታና ብድር ያሰባስባል፣ ይደራደራል፣ ይፈርማል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣
- ከተለያዩ መንግሥታት ጋር የሚደረገውን የኢኮኖሚ ትብብር እንዲሁም የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ከተቋቋሙ ዓለም ዓቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ የዚህ ዓይነቱ ትስስር በአገሪቱ የኢኮኖሚ አፈፃፀም ላይ የሚኖረውን ውጤት ይከታተላል፣
- የፌዴራል መንግሥት አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል ይጠብቃል፣
- የአገሪቱን የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ያስተባብራል ይቆጣጠራል፣
- የካርታና እና የስታትስቲክስ ሥራዎችን በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት

9. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚንስትሮች ምክር ቤት ሆኖ በሚኒስቴር እና በሦስት ሚኒስቴር ዴኤታ ተዋቅሯል:: ስድስት ዳይሬክቶሬቶች እና እስትራቴጂክ ዕቅድ ሥራ አመራር ጽ/ቤት ቀጥታ በሚኒስትሩ የሚመሩ ሲሆን በመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ዘርፍ ሚንስትር ዴኤታ ሥር አራት ዳይሬክቶሬቶች፣ እንዲሁም በውጭ ሀብት ግኝትና አስተዳደር ዘርፍ ሚንስትር ዴኤታ ሦስት ዳይሬክቶሬቶችና ሁለት ጽ/ቤቶች የተዋቀሩ ሲሆን በልማት ዕቅድና የኢኮኖሚ አስተዳደር ዘርፍ ሚንስትር ዴኤታ ስር ደግሞ ስድስት ዳይሬክተሮች

ተዋቅረዋል፡፡ የዚህ ክዋኔ ኦዲት አካባቢ ከበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በቀጥታ ይገናኛል፡፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ዳይሬክቶሬቶች መካከል በተጨማሪ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እና የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ ተጠሪነታቸው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ነው፡፡ መ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደለት በጠቅላላው 855 የሰው ሀይል ሲሆን ከዚህም ውስጥ ለበጀት ዝግጅትና አስተዳዳር ዳይሮክቶሬት የተፈቀደው 47 የሰው ሀይል ቢሆንም ሚኒስትሩንና ሚኒስትር ዴኤታዎችን ጨምሮ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በጠቅላላ በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል እስከ ህዳር/2009 ዓ.ም 554 (63%) ሰራተኞች ሲሆኑ የበጀት ዝግጅትና አስተዳዳር ዳይሬክቶሬት ደግሞ 25 (53%) መሆናቸው ከሰው ሀብት ልማት ሪከርድና ጠቅላላ አገልግሎት የስራ ሂደት ከተሰበሰበ መረጃ ለማውቅ ተችሏል፡፡

የፋይናንስ ምንጭ

10. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥራውን የሚያንቀሳቅሰው ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት ሲሆን በ2006፤ 2007 እና 2008 በጀት ዓመታት ለሚያከናወናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ እንደቅደም ተከተላቸው ብር 414,814,055.43፤ ብር 548,767,509.22 እና 596,309,482.00 በድምሩ ብር 1,559,891,046.65 ያህል ከመንግስት ጸድቆ ለሚተገበሯቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ የተመደበለት ሲሆን ከተመደበለት በጀት ውስጥ በ2006 ዓ.ም ብር 398,003,326.32/96%/፣ በ2007 ዓ.ም ብር 513,898,730.92 /94%/ እና በ2008 ዓ.ም ብር 488,724,632.00 /82%/ በድምሩ ብር 1,400,626,689.06 በስራ ላይ አውሏል፡፡

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሥራ ሂደት መግለጫ

11. የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ የሶስት ዓመት ድጎማ ግምት ማሳወቅ፣ የባለበጀት መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት ጣሪያ ማሳወቅ፣ መ/ቤቶች በተሰጣቸው የበጀት ጣሪያ መሠረት ዓመታዊ የበጀት ጥያቄ እንዲያቀርቡ ጥሪ ማድረግና የበጀት ጥያቄያቸውን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ እንዲያቀርቡ ማድረግ/መከታተል፣ በቀረበው የበጀት ሠነድ ላይ የታዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችንና የበጀት አቀራረቡን በተመለከተ

የበጀት ስሚ ማካሄድ፣ ረቂቅ የበጀት ድጋፍ ማዘጋጀት፣ ረቂቅ የበጀት ድጋፍ ሠነድ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ማቅረብ፣ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በጀት ማፀደቅና መፍቀድ፣ የፀደቀውን በጀት ለአስፈፃሚ መ/ቤቶች ማሳወቅ፣ በፀደቀው በጀት መሰረት የሥራ መርሐ ግብር ማዘጋጀት(በአስፈፃሚ መ/ቤቶች)፣ የፀደቀውን በጀት በሥራ ላይ ማዋል፣ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች መቀበል እና ግምገማ ማድረግ ናቸው፡፡

የኦዲቱ አላማ

12. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ሀብትን ከውጤት ጋር ለማስተሳሰር እየተደረገ ያለውን ጥረት ለማገዝ እና የመሠረተ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥን ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን እንዲሁም ለፕሮግራሞችና ለካፒታል ፕሮጀክቶች የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተል የተዘረጋውን ሥርዓት በመገምገም በአሠራር ላይ ክፍተቶች ከታዩ ደግሞ ክፍተቶቹ እንዲቀረፉ የሚሆን የማሻሻያ ሃሳብ ለመስጠት እና ተጠያቂነትን ለማስፈን ማገዝ ነው፡፡

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

13. ከላይ የተመለከተውን የኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ እና ሁለት የንዑስ ኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Sub audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም፡-

    1. የባለበጀት መ/ቤቶች ያዘጋጁት የፕሮግራም በጀት በተያዘለት ጊዜና ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተልና ለመገምገም የተዘረጋው ሥርዓት ጠንካራ መሆኑን እንዲሁም የፕሮግራም በጀት በመተግበር የሚጠበቀው ውጤት የተገኘ መሆኑን ማረጋገጥ፣
    2. የፕሮግራም በጀት አላማዎችን ለማስፈጸም የተዘረጋው ሥርአት፣ ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣
    3. ሚኒስትር መ/ቤቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነትና እና ጠንካራ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ትስስር ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፤

3.1 ሚኒስትር መ/ቤቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣

3.2 ሚኒስትር መ/ቤቱ ዘመናዊና ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

የሚሉ ናቸው፣

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

14. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሦስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች 25 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የተመረጡት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከው አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው በአባሪ 2 ቀርበዋል ፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

15. ኦዲቱ የሚከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ የተሰራውን ሥራ ሲሆን ኦዲቱ በዋናነት የሚከናወነው በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሆኖ በናሙና የተመረጡ ባለበጀት መ/ቤቶች፣ በናሙና የተመረጡ የክልል ፋይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮዎች የተለያዩ ከሥራው ጋር አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን በመሰብሰብና በመከለስ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና በአካል በማየት ነው፡፡

16. በዚህም መሠረት በናሙና ለተመረጡ ለ6 ባለበጀት መ/ቤቶች (የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የውሃ፣ የመስኖና የኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች)፣ ለ4 ዩኒቨርስቲዎች (አዲስ አበባ፣ ሀዋሳ፣ ዲላና አደማ ዩኒቨርስቲዎች) እና ለክልል ፋይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮዎች (የኦሮሚያና የደቡብ ክልል) በመገኘት ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስ እና በመተንተን የክዋኔ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

ሀ. የባለበጀት መ/ቤቶች ያዘጋጁት የፕሮግራም በጀት በተያዘለት ጊዜና ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተልና ለመገምገም የተዘረጋው ሥርዓት ጠንካራ መሆኑን እንዲሁም የፕሮግራም በጀት በመተግበር የሚጠበቀው ውጤት የተገኘ መሆኑን በተመለከተ፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለበጀት መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት መርሐ ግብርና የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን በማንዋሉ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲያቀርቡ ማድረጉን በተመለከተ፣

17. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለበጀት ዓመቱ የታቀዱ ውጤቶችና ግቦች መሳካታቸውን ለመደበኛ እንዲሁም ለካፒታል ፕሮጀክቶች የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተል በፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ማንዋል በተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ባለበጀት መ/ቤቶች የድርጊት መርሐ ግብራቸውንና የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

18. ይሁን በናሙና በታዩት 4 ዩኒቨርስቲዎች (ዲላ፣ አዳማ፣ አዲስ አበባ እና ሀዋሳ ዩኒቨርስቲዎች) እና 6 ባለበጀት መ/ቤቶች (የኢትዮጵያ መንገድ ባለስልጣን፣ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር) ውስጥ ከመንገዶች ባለስልጣን በስተቀር የተቀሩት 9 መ/ቤቶች መርሐ ግብራቸውን በማንዋሉ መሰረት ከሐምሌ 8-30 መቅረብ ቢኖርበትም ከ15 እስከ አንድ ወር አዘግይተው የሚያቀርቡ መሆኑን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተላኩት እና በኦዲት ቡድኑ ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. እንዲሁም የማስፈጸም አቅምን ያላገናዘበ መርሃ ግብር የሚያቀርቡ መ/ቤቶች ያሉ ሲሆን በ2007 የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ እና የውሃ፣ መስኖና ኤሌትሪክ

ሚኒስቴር፣ በ2008 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ፣ የጎንደር ዩኒቨርስቲ፣ የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ለአብነት የሚገለጹ ሲሆን፣

20. በተጨማሪም በዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ላይ ሰፊ ልዩነት ያለባቸው መ/ቤቶች መኖራቸው ማለትም በሚያቀርቡት ሪፖርት ላይ በፋይናንስና በፊዚካል አፈጻጸሞች መካከል የሚታየው ሰፊ ልዩነት ያላቸው መ/ቤቶች ያሉ ሲሆን ከመ/ቤቶቹ መካከል የብሔራዊ ሥነ ልክ፣ የኢትዮጵያ ኘሮስ ድርጅት እና የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሚገኙበት ሲሆን፤ ለማሳያ ያህል

- በ2007 የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጣና መጽሔት ዝግጅት በ2007 በጀት ዓመት ከመርሐ ግብሩ አንጻር የፊዚካል አፈጻጸሙ 102.45% ሲሆን የፋይናንስ አፈጻጸሙ ግን 81.76% መሆኑ፣
- በ2008 በጀት ዓመት ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ቴክኖሎጂ ልማት በንዑስ ፕሮግራሙ ሥር አምስት ውጤቶች የታቀፉ ሲሆን ምንም እንኳ የአምስቱም ውጤቶች ፋይናንስ አፈፃፀም ከዕቅድ በታች /72.9%/ቢሆንም በውጤት 3 ላይ የታየው የ42.07% የፋይናንስ አፈፃፀም ግን የንዑስ ፕሮግራሙን የፋይናንስ አፈፃፀም በእጅጉ እንዲወርድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል በአንጻሩ የፊዚካል አፈጻጸምንም በተመለከተ በቅደም ተከተል የ184.31%፣ የ100.67% ፣የ100%፣ የ180% እና የ259.38% መሆኑ ሆኖም በውጤት 3 ላይ የታየው በ42.07% የፋይናንስ አፈፃፀም እንዴት የ100% የፊዚካል አፈፃፀም ሊገኝ እንደቻለ በሪፖርቱ የተገለፀ ነገር ባይኖርም በፋይናንስና በፊዚካል አፈፃፀም መካከል የታየው ከፍተኛ ልዩነት ወይም አለመጣጣም በዕቅድ አዘገጃጀቱ ላይ ክፍተት መኖሩን የሚያመላክቱ መሆኑን መገንዘብ መቻሉንና በዕቅድ አዘገጃጀት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ማዘጋጀት ለዓመቱ የውጤቶች ግብ ስኬት አስተዋጽኦ መኖሩን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የመ/ቤቶች የሪፖርት አፈጻጸም ግምገማ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል::

21. የአፈጻጸም ሪፖርቶችን በተመለከተ የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን በወቅቱ የማይልኩ፣ የተሟላ/የፋይናንሻል አፈጻጸም ላይ ብቻ የተመሰረተ/ና ጥራቱን ያልጠበቀ ሪፖርት የሚልኩ መ/ቤቶች መኖራቸው በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት መ/ቤቶች በቃለ-

መጠይቅ፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2006-2008 በጀት ዓመት የመ/ቤቶች የአፈጻጸም ግምገማ እና የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. በተጨማሪም የፋይናንስ አፈፃጸም ላይ ብቻ የተመረኮዘ ሪፖርት የሚያቀርቡ መ/ቤቶች ያሉ ሲሆን በ2006 ሁለተኛ ሩብ በጀት ዓመት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ፣ የሀረማያ ዩኒቨርስቲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት፣ በ2007 በጀት ዓመት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የሀረማያ ዩኒቨርስቲ፣ የጐንደር ዩኒቨርስቲ የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ፣ የወሎ ዩኒቨርስቲ፣ የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ፣ የወለጋ ዩኒቨርስቲና የመደወላቡ ዩኒቨርስቲ፣ እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የሀረማያ ዩኒቨርስቲ፣ የመቱ ዩኒቨርስቲ፣ ጐንደር ዩኒቨርስቲ፣ ጋምቤላ ዩኒቨርስቲ፣ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣ የጅጅጋ ዩኒቨርስቲና ወሎ ዩኒቨርስቲ የፊዚካል ሪፖርት እንዳላቀረቡ ከተከለሱ መረጃዎች ታውቋል፡፡

23. በተመሳሳይ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ካላቀረቡ መ/ቤቶች መካከል በ2006 በጀት ዓመት የአክሱም ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ በ2007 በጀት ዓመት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የወለጋ ዩኒቨርስቲና የመደወላቡ ዩኒቨርስቲ እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ጋምቤላ ዩኒቨርስቲ እንደሚገኙበት ታውቋል፡፡

24. 2007 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ግብርና ኢንስቲትዮት የፎገራ የሩዝ ምርምር ማዕከል እና ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት እንደሚጠናቀቅ የሚጠበቀው የፍቼ ዱፕሊኬት ጂን ባንክ ግንባታ አፈፃፀም በሪፖርቱ አለመካተቱ፣

25. በተመሳሳይ መልኩ በ2008 በጀት ዓመት የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በግብርና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሚካሄዱ ግንባታዎች የአፈፃፀም ሪፖርት አለመገለፁ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የምርምር ማዕከል ግንባታና የሌሎችም ግንባታዎች አፈጻጸም ሪፖርት በዝርዝር ቢያቀርብም የሁለት ፕሮጀክቶችን መርሃ ግብርና የተደረሰበትን የፊዚካል ሥራዎችን ደረጃንና ወጪዎች እስከ በጀት ዓመቱ ድረስ የሚገልጽ ሪፖርት አለመቅረቡ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

ኢንስቲትዩት በ2008 እና በ2007 በጀት ዓመት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ስለ ከፒታል ፕሮጀክቱ ቅጽ ሪማ2ን በተመለከተ በፕሮጀክቱ ሥር ያሉትን ዋንኛ የሆኑትን ተግባራት በመለየት ማሳየት አለመቻሉ፣

26. በ2008 ዓ.ም. አብዛኛው መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈፃፀም ሪፖርት በአብዛኛው የክትትል ዓላማን የማያሟላ/ማለትም የፊዚካል አፈጻጸም የቀረበላቸውም በአብዛኛው በሪፖርቱ የተጠቀሰው የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት እንጂ የውጤቶች እና የፕሮጀክቶች አፈፃፀም አለመሆኑ/ ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. እንዲሁም የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ማንዋል ገጽ 73 ላይ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በተዘጋጀው መርሃ-ግብር መሠረት የየሩብ ዓመት እና ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት መዘጋጀት እንደሚኖርበት የሚገልጽ ቢሆንም ከመርሐ ግብሩ ውጭ ወይም መርሃ ግብርን መሰረት ያላደረገ ሪፖርት የሚያቀርቡ መ/ቤቶች ያሉ ሲሆን በ2007 በጀት ዓመት ግብርና ሚኒስቴር፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የምርት ገበያ ባለሥልጣንና ወላይታ ዩኒቨርስቲ እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ የግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ የውሃ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ፣ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እንሚገኙበት ታውቋል፡፡

28. በናሙና በታዩ በሁሉም መ/ቤቶች በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ መርሐ ግብርም ሆነ ሪፖርት የሚዘገይበት ምክንያት ሲገልጹ ለተለያየ አካላት ሪፖርት የሚያቀርቡ በመሆኑ እንደሆነና በማንዋሉ መሰረት መርሐ ግብርም ሆነ የሪፖርት አፈጻጸማቸውን የማያዘጋጁበት ምክንያት ደግሞ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰጠው ስልጠና በቂ ባለመሆኑና የፕሮግራሙ ባለቤት ለሆኑት አመራሮች የማይሰጥ ስለሆነ የአቅም ክፍተት እና ትኩረት የማይሰጠው በመሆኑ በሚፈልገው ደረጃ በጥራት ማቅረብ አለመቻላቸውን የገለጹ ሲሆን በተጨማሪም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሮግራም በጀት እየተሰራበት ባለመሆኑ የፋይንሻል አፈጻጸም ብቻ እንደሚልክ ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጭራሽ ምንም ሪፖርት የማያቀርቡት መ/ቤቶችን በጀት እንደማይለቁላቸው ነገር ግን መርሐ

ግብራቸውንም ሆነ የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን በወቅቱ የማይልኩ መ/ቤቶች መኖራቸውን እንዲሁም እላይ በታየው ችግር መ/ቤቶች በጀት መጠየቁ ላይ እንጂ የፕሮግራም ውጤቶች ላይ ትኩረት የማይሰጡ መሆናቸውና ከመርሐ ግብር ዝግጅቱ ጀምሮ መ/ቤቶች የአቅም ክፍተት በመኖሩ ሪፖርት በመርሐ ግብር መሰረት የማይልኩ በመሆኑ አሠራር ላይ ክፍተት መፈጠሩንና በ2008 ዓ.ም የተላከው የአብዛኛው መ/ቤቶች የአፈጻጸም ሪፖርት ለግምገማ የሚያመች ባለመሆኑ መቸገራቸውን የአቅም ክፍተት መሆኑ በመ/ቤታቸው ስለታመነበትም ችግሩን ለመፍታት በዚህ ዓመት ሰፋ ያለ የተግባር ስልጠና መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

30. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለበጀት መ/ቤቶች ሪፖርት በወቅቱና ለግምገማ በሚያመች መልኩ እንዲያቀርቡ አስቀድሞ የፕሮግራም በጀት መርሐ ግብርና አፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት ላይ አስፈላጊውን ስልጠና አለመስጠቱ ተቋማቱ በመርሐ ግብራቸው መሰረት ማከናወናቸው ላይ ያለውን የክትትልና የግምገማ ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የፕሮግራም በጀትን ተግባራዊ ያደረጉ ባለበጀት መ/ቤቶች በመርሃ ግብራቸው መሠረት ሥራ አፈጻጸማቸው ላይ ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤

31. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለበጀት መ/ቤቶች የታቀዱት ግቦች የደረሱበት ደረጃና አፈጻጸም ካስቀመጡት መርሃ ግብር አንጻር በየጊዜው ክትትል በማድረግ እና በተገኙ ልዩነቶች ላይ በወቅቱ ማሻሻያ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል።

32. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2007 ዓ.ም. እና በ2008 ዓ.ም በተከታታይ 155 እና 165 ባለበጀት መ/ቤቶች ውስጥ የ114 እና 124 መ/ቤቶች ግምገማ ቢያደርግም የተቀሩት 41 መ/ቤቶች በሁለቱም ዓመት ግምገማ ያላደረገ መሆኑ፣ በሦስቱም ዓመት በየሩብ ዓመቱ የመ/ቤቶችን ሪፖርት ግምገማ ማካሄድ ቢኖርበትም ባለጀበት መ/ቤቶች በ2006 ዓ.ም. የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 53 በሁለተኛ ሩብ ዓመት 45 መ/ቤቶች ሪፖርት ያለቀረቡ በመሆኑ ግምገማ ያልተደረገባቸው ሲሆን በ2007 ዓ.ም. የመጀመሪያና ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ያላቀረቡ መ/ቤቶች በመኖራቸው ከ155 ባለበጀት መ/ቤቶች በተከታታይ የ100 እና የ108 መ/ቤቶች ሪፖርቶች የተገመገሙ በመሆኑ የግምገማው አፈጻጸም 65 በመቶና 70 በመቶ መሆኑ እንዲሁም በሦስቱም በጀት ዓመት የሦስተኛ ሩብ ዓመት ማለትም የ9 ወር የመ/ቤቶች አፈጻጸም ግምገማ

ሪፖርት በወቅቱ አለመዘጋጀቱ በኦዲቱ ወቅት ከበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

33. በ2008 ዓ.ም. አብዛኛው መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈፃፀም ሪፖርት የክትትል ዓላማን የማያሟላ/ማለትም የፊዚካል አፈጻጸም የቀረበላቸውም በአብዛኛው በሪፖርቱ የተጠቀሰው የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት እንጂ የውጤቶች እና የፕሮጀክቶች አፈፃፀም አለመሆኑ/ የ2008 ዓ.ም. የመ/ቤቶች አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም ለሁሉም መ/ቤቶች አፈጻጸም ተገምግሞ በጽሁፍ ግብረ መልስ አለመሰጠቱ እና መ/ቤቶችን ተጠያቂ ከማድረግ አንጻር የግምገማ ውጤት ለውስጥ አሰራር ከመጠቀም ውጭ ለየትኛው አካል የማይቀርብ መሆኑን በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. በናሙና በታዩት ባለበጀት መ/ቤቶች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመርሐ ግብር አንጻር አፈጻጸማቸው እየተገመገመ ባለው ልዩነት ላይ በቃል እንጂ በዝርዝርና በጥልቀት በጽሑፍ ግብረ መልስ የማይሰጣቸው መሆኑን፤ በቃል የሚነገራቸውም ግብረ መልስ አልፎ አልፎ እንጂ ተከታታይነት ባለው መልኩ አለመሆኑንና በመርሐ ግብሩ መሰረት መሄዳቸው ያለው የክትትል ሥርዓት ዝቅተኛ መሆኑን የየመ/ቤቱ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

35. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከመርሐ ግብራቸው አንጻር የመ/ቤቶችን አፈጻጸም ለመገምገም እንደሚሞከር ነገር ግን ከላይ በተራ ቁጥር 29 ላይ እንደተገለጸው መ/ቤቶች ከመርሐ ግብር እስከ አፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት ላይ የአቅም ክፍተት በመኖሩ ሪፖርት በመርሐ ግብር መሰረት የማይልኩ በመሆኑ እና በወቅቱ የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን የማያቀርቡ መ/ቤቶች በመኖራቸው የክትትል ሥራው ላይ ክፍተት መፍጠሩን የገለጹ ሲሆን ሪፖርቶች ተገምግመው ግብረ መልስ የማይሰጥበት ምክንያት ወደ 165 መ/ቤቶች በጽሑፍ ግብረ መልስ መስጠቱ እራሱን የቻለ ሥራ በመሆኑ ካለው የሰው ኃይል አንጻር ይህን መስራት እንዳልቻሉ በተጨማሪም እንደበጀት ስሚው ተጠያቂ ከማድረግ አንጻር የአፈጻጸም ሪፖርት ግምገማው ለየትኛውም አካል እንደማይቀርብ እና ግኝቱ ትክክል በመሆኑ ለወደፊቱ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራበት ገልጸዋል፡፡

36. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመ/ቤታችን በተላከው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው መልስ መ/ቤቶች ባዘጋጁት መርሃ ግብር ላይ ስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ በጹሁፍ ግብረ መልስ ባይሰጥም በተለያዩ ዘዴዎች ማለትም በኢ-ሜይል፣ በቃል እና በግንባር በመጥራት መርሃ ግብሩን ላዘጋጁት ባለሙያዎች አስተያየታቸው እንዲደርሳቸው እንደሚደረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም አሻሽለው በድጋሚ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ እንደሚደረግ እንዲሁም የ9 ወር የሪፖርት ግምገማ አለመደረጉን በተመለከተ የበጀት ዝግጅት ወቅት በመሆኑ የፕሮግራም በጀት ክትትልና ግምገማ ለማድረግ ቢታቀድም ትኩረት የነበረው በበጀት ዝግጅቱ ላይ በመሆኑ ሊከናወን አለመቻሉ ታሳቢ ቢደረግ በሚል ገልጸዋል፡፡

37. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በላከው መልስ ይህን ቢልም ከላይ እንደተገለጸው ባለበጀት መ/ቤቶች አልፎ አልፎ እንጂ ቀጣይነት ባለው መልኩ ግብረ መልስ እንደማይሰጣቸው የገለጹ ሲሆን ሪፖርት በወቅቱና ለግምገማ በሚያመች መልኩ እንዲያቀርብ በማድረግ ከላይ በተገለጹት በሁሉም መ/ቤቶች እና የሦስተኛው ሩብ ዓመት ግምገማ አለማድረጉ እንዲሁም በዝርዝር በጽሁፍ ግብረ መልስ አለመስጠቱ ተቋማቱ በመርሐ ግብራቸው መሰረት መሄዳቸው እና የተመደበላቸው በጀት ለተለመለት አላማ በአግባቡ መዋሉን የመከታተል ሥራው ክፍተት መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡

ሚኒስቴር መቤቱ መ/ቤቶችን የመስክ ጉብኝት እና ቅኝት ለማድረግ
<u>መርሃ ግብር በማዘጋጀት በመርሃግብሩ መሰረት መከታተሉን በተመለከተ</u>፤

38. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸምን አስመልክቶ ወቅታዊነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ በድንገት ወይም በተወሰነ ጊዜ ክትትል ለማድረግ መርሃ ግብር ሊያዘጋጅና በመርሃግብሩ መሰረትም ጉብኝት እና ቅኝት በማድረግ ሊከታተል፣ በወቅቱ የታዩ የአሠራር ድክመቶችና ጥንካሬዎች በመለየት የእርምት እምርጃዎችን ሊወስድና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ውጤታማነትን አስመልክቶ ባለበጀት መ/ቤቶችና ፕሮጀክቶች ላይ ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ በማካሄድ በአሠራር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል የክትትልና የግምገማ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ ቢጠበቅበትም የፕሮግራም

በጀትን መተግበር ከጀመሩ 155 ያህል ተቋማት በ2006 እና በ2007 ዓ.ም. ከጥቅምት እስከ የካቲት ክትትል ለማድረግ በአመታዊ ዕቅዱ ላይ ቢገልጽም ከነዚህ ተቋማት ምን ያህሉን ፕሮጀክቶች እና የትኞቹን ፕሮጀክቶች ላይ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ እንደታሰበ የሚያሳይ የድርጊት መርሃ ግብር ያላዘጋጀ መሆኑን ጉዳዩን አስመልክቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

40. በ2008 በጀት ዓመት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀት ተግባራዊ ካደረጉ 165 ተቋማት በ5ቱ ላይ ብቻ ማለትም በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ፣ በግብርና ዘርፍ፣ በፌዴራል ፖሊስ፣ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እና በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር /በመስኖ ግድቦች ግንባታ ላይ/ በጠቅላላው 23 ፕሮጀክቶች ለማየት የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጀ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2006፣ በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት ወቅታዊ ክትትልና ድጋፍ ማድረጉን አስመልክቶ ኦዲት ሲደረግ በ2006 ዓ.ም. የመስክ ክትትል ስለማድረጉ በኦዲቱ ወቅት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃ አልተገኘም፡፡ በ2007 በጀት ዓመት ከ155 ባለበጀት መ/ቤቶች በሦስቱ እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት በመርሐ ግብር ከያዛቸው 5ት መ/ቤቶች ሦስቱ ላይ ብቻ የመስክ ክትትል ያደረገ ሲሆን በሌሎች መ/ቤቶች ግን ትኩረት ሰጥቶ የማያደርግ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ከከለሳቸው መረጃዎችና በናሙና ተመርጠው በታዩት መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የመስክ ጉብኝት ካደረገባቸው ተቋማት ካላቸው የፕሮጀክቶች ብዛት አንጻር አፈጻጸሙ ሲገመገም፡-

የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው መ/ቤቶች	በመ/ቤቱ ያሉ ፕሮጀክቶች ብዛት	የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው ፕሮጀክቶች ብዛት		አፈጻጸሙ ካለው የፕሮጀክት ብዛት አንጻር በመቶኛ ሲገመገም		ምርመራ
		በ2007	በ2008	በ2007	በ2008	
የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን	250	9	2	04%	.008%	
የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር	50	2	2	.04%	.04%	
የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች	4	-	1	-	25%	በ2007 ዓ.ም. አልተደረገም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ	10	3	-	30%	-	ችግር የነበረባቸውና ተቋርጠው የነበሩ ሶስት ፕሮጀክቶች ላይ የተደረገ ቢሆንም ከዛ በፊትም ሆነ በ2008 ዓ.ም. የመስክ ጉብኝት አልተደረገም፣

41. በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመ/ቤታችን በተላከው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጠው መልስ የመስክ ጉብኝቱ አብዛኛው መ/ቤቶች ላይ የማይደረገው ለክትትል ሥራ ለብቻው ክፍል ባለመኖሩ፣ የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ እና በሌላ ሥራ ላይ ያሉ ባለሙያዎች ደርበው ሥራውን የሚሰሩ በመሆኑ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

42. ከላይ እንደተገለጸው የመስክ ጉብኝቱ ካሉት ኘሮጀክቶች አንጻር በጣም ጥቂቱ ላይ እና ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚካሄድ ባለመሆኑ እና ከሦስት መ/ቤቶት በስተቀር በተቀሩት መ/ቤቶች ላይ የተመደበው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉንና በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መጠናቀቃቸው የማረጋገጥ ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ከማሳደሩ በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥራ ክትትል ወቅት ሊስተካከሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች በወቅቱ በመለየት የተቋማቱ ኘሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ወቅታዊ ድጋፍ ለማድረግ አላስቻለም።።

<u>የኘሮጀክቶች አፈጻጸም መ/ቤቶች ባቀረቡት መርሐ ግብር መሰረት መሆኑን በተመለከተ</u>፤

43. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለበጀት መ/ቤቶች የሚገነቡት ኘሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ማለቃቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

44. በመሆኑም በፌዴራል ደረጃ መንግስት ከፍተኛ በጀት የሚመድበው በካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው በመርሐ ግብራቸው መሰረት ያለው የክትትል ሥራ አነስተኛ በመሆኑ እና በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት በአራት መ/ቤቶች ላይ ብቻ እና በአራቱ መ/ቤቶች ካሉት 314 ኘሮጀክቶች በ19ኙ/.06%/ ላይ ብቻ የመስክ ጉብኝት በመደረጉ የኘሮጀክት አፈጻጸማቸው በናሙና ከታዩት የ8 መ/ቤቶች (የአዲስ አበባ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና የዲላ ዩኒቨርስቲዎች፣ የውሃ፣ መስኖና

ኤሌትሪክ ሚኒስቴር፣ የመንገዶች ባለስልጣን፣ የማረሚያ ቤቶች እና የትምህርት ሚኒስቴር) ፕሮጀክቶች በመርሐ ግብራቸው መሰረት ስለማለቃቸው በተደረገ የኦዲት ምርመራ፡-

45. መንገዶች ባለስልጣን በመጀመሪያው የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሊሰሩ የታሰቡ ከ20 በላይ ፕሮጀክቶች ወደ 2008 ዓ.ም. በመሸጋገራቸውና ነባር ፕሮጀክቶች በመኖራቸው ምክንያትም አዲስ ፕሮጀክት አለመጀመሩ፣ በተጨማሪም በናሙና ከታዩት ሦስት ፕሮግራሞች ውስጥ የዋና መንገዶች ማጠናከር ፕሮግራም ካሉት 12 ፕሮጀክት 7ቱ በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ ሲሆን ሁለቱ በ2005፣ ሁለቱ በ2006፣ ሦስቱ ደግሞ በታህሳስ፣ በሰኔና በሐምሌ 2007 ዓ.ም. መጠናቀቅ የነበረባቸው ቢሆንም ከሦስት እስከ አንድ አመት ዘግይተው በ2008 ዓ.ም. መጠናቀቃቸው፣

46. እንዲሁም የዋና መንገዶች ደረጃ ማሻሻል ፕሮግራምን በተመለከተ 9 ፕሮጀክቶች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አምስቱ ሐዋሳ ጭኮና ይርጋ ጨፌ የካቲት 2008 ዓ.ም. ማለቅ የሚገባቸው ቢሆንም ሥራው እንዲቋረጥ የተደረገ ሲሆን ይርጋጨፌ ሀገረማርያም፣ በደሌ - መቱ/ሎት 1/ እና በደሌ - መቱ/ሎት 2/ የካቲትና ሚያዚያ 2008 ዓ.ም. ማለቅ ቢገባቸውም አፈጻጸማቸው ግን ደካማ /50% በታች/መሆኑ፣

47. አገናኝ መንገዶች ደረጃ ማሻሻል ፕሮግራም በተመለከተ 51 ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በ2008 ከተጠናቀቁት 14 ፕሮጀክቶች 11ዱ /ግንደበር - ጎቤንሳ፣ አረቅት - ሆሳዕና፣ወልቂጤ - አረቅት፣ሰርጥ መንደር - ወርኢ፣ማይጸብሪ - ሽሬ፣ መቀሌ - ሰርጥ መንደር፣ዛሪማ - ማይጸብሪ ፣ኢርባሞዳ - ዋደራ፣አይራ - ጫንቃ፣ መቀናጅ - አይራ፣ ጫንቃ - ዶምቢዶሎ/ በወቅቱ ያልተጠናቀቁ ሲሆን ከሰኔ 2006-ሚያዚያ 2007 በተለያየ ወር ማለቅ የሚገባቸው ቢሆንም በ2008 መጠናቀቃቸው፣

48. በዲላ ዩኒቨርስቲ ካሉት 28 ፕሮጀክቶች ውስጥ አሥራ ዘጠኙ /68/ በመቶ በተያዘላቸው ጊዜ ያላለቁ ሲሆን ከተገለጹት ውስጥ በ2008 ዓ.ም በመጠናቀቅ ላይ ካሉትና ከ80 በመቶ በላይ አፈጻጸም ያሳዩት የተማሪዎች ማደሪያ፣ ካፍቴሪያ፣ መማሪያ መጋዘን እና የምድረ ግቢ ሥራ በ2002 ዓ.ም.፣ የአጥር ግንባታ በ2006 ዓ.ም.፣ የተማሪዎች የሰራተኞችና የመምህራን የመማሪያና የማደሪያ ብሎኮች በ2006 ዓ.ም.፣ የትሪትመንት ፕላንት እና የተማሪዎች ማደሪያ ካፍቴሪያ በ2007 ማለቅ ቢኖርባቸውም ከ1 እስከ 5 አመት ቆይተው በ2008 ዓ.ም. መጠናቀቅ ላይ

መድረሳቸው፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ካሉት አስር ፕሮጀክቶች ዘጠኙ ፕሮጀክት በጊዜ ሰሌዳቸው መሠረት ያልተጠናቀቁ መሆኑ እና በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ በናሙና ከታዩት 41 ፕሮጀክቶች ውስጥ 34 የሚሆኑ ፕሮጀክቶች በመርሐ ግብሩ መሰረት ያልተጠናቀቁ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት ከየመ/ቤቱ ከተሰበሰቡና ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

49. በተጨማሪም በውሃ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ ከመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልገሎት አሰጣጥ አንፃር ከፍተኛ ግብ የተጣለባቸውና ከፍተኛ በጀት የተመደበላቸው የመስኖ ልማት፣ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የውሃ ሀብት አስተዳደርና የኢነርጂ ልማት ፕሮግራሞች ሲሆኑ በ2008 ዓ.ም. ብቻ ጠቅላላ ብር 5,737,785,935 (አምስት ቢሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ሰባት ሰባት መቶ ሰማንያ አምስት ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አምስት ብር) በጀት የተመደበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 5,687,785,940(አምስት ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ብር) /99%/ ለካፒታል የተመደበ እና እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም. የመደበኛውን ጨምሮ ብር 5,011,862,795.00 (አምስት ቢሊዮን አሥራ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ብር)/87.83 በመቶ/ የተጠቀመ ሲሆን ካስቀመጠው መርሃ ግብር አንጻር ካሉት 50 ፕሮጀክቶች ሃምሳውም ፕሮጀክቶች በጊዜ ሰሌዳቸው መሰረት ያልተጠናቀቁ እና ከዚህ ውስጥ 17 ፕሮጀክቶች ፊስካል አፈፃፃማቸው ከ50% በታች መሆኑ ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከላይ ከተገለጹ የተቀሩት የየመ/ቤቱ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

50. እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመለከታቸው መ/ቤቶች የሚቋረጡ ፕሮጀክቶች መኖራቸው በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከነዚህም ውስጥ፤

- በአዳማ ዩኒቨርስቲ በሐብታሙ ኢንተርናሽናል የንድፍና ምህንድስና ምክር አገልግሎት ኃላፊነቱ የተ.የግ.ማህበር የሚገነቡ የስብሰባ አዳራሽ፣ የማዕከላዊ አስተዳደር ህንፃዎችና የስፖርት አካዳሚ ፕሮጀክቶች ሰኔ 2005 ዓ.ም. ተጀምረው ሰኔ 2008 ዓ.ም. የሚጠናቀቁ እንዲሁም ፊዚካል አፈጻጸማቸውም 74 በመቶ

ቢሆንም የሥራ ተቋራጩ በገባቸው ውሎች መሰረት ኃላፊነቱን ባለመወጣቱና ከውሉ ውጭ ተጨማሪ ብር 115,000,000 በመጠየቁ የኦዲት ቡድኑ ለኦዲት ሥራው በዩኒቨርስቲው በተገኘበት በሐምሌ ወር የግንባታ ሥራው እንደተቋረጠ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- እንዲሁም የአሰላ የጤና ሳይንስ መማሪያ አዳራሽ፣ የላብራቶሪ ህንጻዎች ኘሮጀክትና የአሰላ 1ኛ ደ/ት/ቤት የተጨማሪ መማሪያ ክፍሎች ግንባታ በሰኔ 2004 ተጀምሮ መስከረም 2007 መጠናቀቅ ቢኖርበትም እስከ 2008 በጀት አመት ያልተጠናቀቀ፣ ለመገንባት ውል የገቡ ተቋራጮች በውላቸው መሰረት ባለመስራታቸውና በታቀደው ጊዜ መሰረት ሥራቸውን ባለማገባደዳቸው ኘሮጀክቶቹ የተቋረጡ ሲሆን ተቋራጮቹ ያለባቸውን የገንዘብ ዕዳ ለዩኒቨርስቲው እንዲመልሱ፣ የኘሮጀክቶቹን ሥራዎች እንዲያስረክቡና ሳይቱን ለቀው እንዲወጡ ትዕዛዝ ቢሰጥም ዕዳ ለመክፈልም ሆነ ሥራዎችን ለማስረከብ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት እንደቀረበ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በተመሳሳይ መልኩ በዲላ የኮንዶሚኒየም እና የምድረ ግቢ ሥራ ብር 18,768,263.04 የተመደበ ሲሆን በ8/8/07 ተጀምሮ በ20/03/08 የሚያልቅ ሲሆን እስከ ሚያዚያ 8/2008 ያላለቀና 35 በመቶ ብቻ አፈጻጸም ያለው ወይም ከ13 ብሎክ ውስጥ 3 ብሎክ ብቻ የተሰራና የኦዲት ቡድኑ ለኦዲት በሄደበት ወቅት ኮንትራክተሩ ማህበራዊ ችግር አጋጥሞታል በሚል ሥራው እንደቆመ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 5 ኪ.ሜ. ዩኒቨርስቲዎችን የሚያገናኝ የውስጥ ለውስጥ የአስፋልት መንገድ ሥራ ብር 93,715,287.47 የተመደበለት ቢሆንም ለ8 ወር ያህል ከካሳ ክፍያ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ባለው ሥራ ማለትም ከመብራት ውሃ መነሳት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ወደ ሥራ መግባት እንዳልተቻለ ታውቋል፡፡
- መንገዶች ባለሥልጣን የዋና መንገዶች ደረጃ ማሻሻል ኘሮግራም ውስጥ ሁለት ኘሮጀክቶች መካከል ሐዋሳ ጭኮ 66 ኪሎ ሜትር መንገድ፣ ሚያዝያ 2005 ዓ.ም. ተጀምሮ በሚያዝያ 2008 መጠናቀቅ ያለበት ቢሆንም እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም. የፊዚካል አፈጻጸሙ 23.5 ሲሆን የኦዲት ቡድኑ የኘሮጀክቶችን አፈጻጸም ለመገምገም በተንቀሳቀሰበት በሐምሌ/2008 ዓ.ም. ሥራው እንዲቋረጥ መደረጉ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የመስክ ጉብኝት ሪፖርት በተገኘ መረጃ የኤሌክትሪክ ምሰሶዎችና የቴሌ ፋይበር ኦኘቲክ በወቅቱ አለመነሳትና

ከዚህ ጋር በተያያዘ የካሳ ክፍያዎች ተከፍለው የቆዩ ቢሆንም ንብረቶቹ አለመነሳታቸው ከፍተኛ ችግር በሥራው ላይ እንደፈጠረ የተገለጸ ቢሆንም በአለታ ጩኮ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ ለአካባቢው ነዋሪ ካሳ በመክፈል ህብረተሰቡን በወቅቱ እንዲነሱና ሥራው እንዲፋጠን ግፊት የተደረገ እና በእነሱ በኩል መደረግ ያለበት እንዳደረጉ ነገር ግን እንደጅምሩ ሥራው በሚፈለገው ፍጥነት ካለመሄዱም በላይ ሥራው መቋረጡን እና ከሌላ አገር ጋር የሚያገናኝ መንገድ እንደመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት አለመሰራቱ በአካባቢው ማህበረሰብም ቅሬታ መፍጠሩን በተጨማሪም የፕሮጀክቱን አፈጻጸም እና ኮንትራክተሩን በውሉ መሠረት ስለማከናወኑ የሚከታተል አካል እንዳልነበረ ገልጸዋል፡፡ የኦዲት ቡድኑ የመንገድ ሥራው የተቆራረጠ ማለትም የተወሰነ ኪሎ ሜትር ከተሰራ በኋላ የተወሰነው ኪሎ ሜትር ያልተሰራ መሆኑን በጎን በኩልም የተወሰነ ሜትር ተሰርቶ የተወሰነ ሜትር መተውን በሥፍራው በአካል በመገኘት ለማየት ችሏል፡፡

- በተመሳሳይ ጭኮ ይርጋ ጨፌ ፕሮጀክት በህንድ የሥራ ተቋራጭ የሚሰራ ሲሆን የፕሮጀክቱ ጠቅላላ የተመደበው ብር 787.7 ሚሊዮን እና በሚያዝያ 2005 ዓ.ም ተጀምሮ በሚያዝያ 2008 ዓ.ም. ማለቅ የሚገባው ቢሆንም እስከ 2008 በጀት ዓመት አፈጻጸሙ 24.3 ከመሆኑም በላይ የሥራ ተቋራጩ ለሥራው የሚሆኑ ዋና ዋና ግብዓቶች በወቅቱ ባለማቅረቡና ሥራውን በውሉ መሰረት ባለመሰራቱ ሥራው መቋረጡ ለማወቅ ተችሏል፡፡

51. ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ እና በተሰጠ መልስ ፕሮጀክቶች በመርሐ ግብራቸው መሰረት አለመሄዳቸውን በተመለከተ በተለይ የውሃና የመስኖ ፕሮጀክቶች ላይ በጣም አስከፊ ችግር መኖሩን እና ፕሮጀክቶች ዲዛይን ቀድሞ ባልወጣበት ሁኔታ ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ፣ ዲዛይን በአግባቡ አለማለቅ፣ አስቀድሞ አለመዘጋጀትና የሥራ ተቋራጭ አቅም አለመኖር እንዳለ የገለጹ ሲሆን መንገዶችን በተመለከተ ፖሊሲው የአገር ውስጥ ተቋራጮች አቅም መገንባትና ማደግ አለባቸው ስለሚል የአገር ውስጥ ተቋራጮችን ማስታመም አስፈላጊ መሆኑን፣ በሥራ ተቋራጮች ምክንያት የሚቋረጡ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የፊተኛውን ሥራ ተቋራጮች ሥራ መገምገምና ወደ አዲስ ለመሄድ ብዙ ሂደት ስለሚኖረው የበፊቱን አስታሞ መሄድ ስለሚቀል በዛ መልኩ እየተሄደበት

መሆኑን ገልጸው በመቀጠልም በአሁኑ ወቅት ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት አስቀድሞ የሥራ ተቋራጮች የበፊት አፈጻጸማቸው እንዲታይ እየተደረገ መሆኑን እና መ/ቤቶች በ2006 ዓ.ም. የነበሩ የነባር ፕሮጀክቶች ማለቅ እንዳለባቸው የተነገራቸው ቢሆንም ነባር ፕሮጀክቶች እስካሁን ካለማለቃቸውም በላይ በነባር ፕሮጀክት ሥራ አዲስ ፕሮጀክቶች እየጨመሩ ስለሚመጡ ብር እየጨመረ መምጣቱን እና ምን እየሰሩ እንዳለ ሪፖርት ካላደረጉ ማለትም በአዲስ መልክ በሪፖርት እስካላካተቱ ድረስ ማወቅ እንዳማይቻል እንዲሁም ካምፓሶችን አራርቆ መሥራት በራሱ ወጪውን ማብዛት ቢሆንም ክልሎች ዩኒቨርስቲን ማስፋፋት ከተማ እንደማስፋፋት ስለሚቆጥሩት ፍላጐት እንዳላቸው በተጨማሪም ሪፈራል ሆስፒታሎች ለማስተማሪያ የሚጠቅሙ ቢሆንም ማህበረሰቡ እንዲታከምበት ሆኖ ተወስኖ እንደሚመጣ እና ለአሰራርም እንተደቸገሩ እንዲሁም አዲስ መ/ቤት የተቀናጀ መሰረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ የተቋቋመ መሆኑንና ለወደፊቱ ካሳ ክፍያን ጨምሮ የሚሰራ ስለሆነ በተለየ የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ የሚመጣውን ችግር እንደሚፈታ ገልጸዋል፡፡

52. ጉዳዩን አስመልክቶ በመ/ቤታችን ለሚኒስትር መ/ቤቱ በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በተሰጠው መልስ በሀዋሳና በዲላ ዩኒቨርስቲ የተጠቀሱት የፕሮጀክቶች ብዛት በአብዛኛው በነባር ፕሮጀክቶች ማጠናቀቂያ ሥራ ያሉ ኮምፖነንቶች መሆናቸው እንዲታወቅ ሲሉ ገልጸዋል፡፡

53. ይህን ቢሉም ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ በትክክል ባለበጀት መ/ቤቶች ሥር ያሉትን ፕሮጀክቶች አለማወቁ እንዲሁም ባለበጀት መ/ቤቶችም ነባር ፕሮጀክቶች ማጠናቀቂያ ሥር አዲስ ፕሮጀክቶችን ማካተታቸው አግባብ ካለመሆኑም በላይ ከላይ የተገለጹት ፕሮጀክቶች ላይ የታዩ ችግሮች የተመደበውን ገንዘብ በአግባቡ ሥራ ላይ እየዋለ ነው ለማለት የማያስችል እና በአገር ሀብት ላይ ከፍተኛ ወጪን የሚያስከትል ነው፡፡

የፕሮግሞች ውጤት ከግብ ስኬት አንጻር መገምገሙን በተመለከተ፤

54. ሚኒስትር መ/ቤቱ የታለመ የውጤቶች ውጤታማነትና የፕሮግራሞች የግብ ስኬት በፕሮግራም በጀት ዘመን ከተጣለው የግብ ስኬት አንጻር በእያንዳንዱ የፕሮግራም በጀት ዓመት የተገኘው ዓመታዊ የግብ ስኬት ምን ያህል እንደሆነ መገምገም ይኖርበታል፡፡

55. ይሁን እንጂ በየዓመቱም ሆነ የሦስት ዓመቱ /ከ2004-2006 በጀት ዓመት/ የመ/ቤቶች ፕሮግራሞች ከግብ ስኬትና ከመጀመሪያው ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንጻር ያመጡት ውጤት እንዳልተገመገመ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

56. በናሙና በታዩ በ4ቱም ዩኒቨርስቲዎች(በዲላ፣ በአዳማ፣ በአዲስ አበባና በሀዋሳ)ና በ6ቱ (በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፣ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር)መ/ቤቶች በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ የፊዚካል አፈጻጸሙ በመቶኛ የደረሰበትን እንጂ ከጣለበት ግብ አንጻር የመጣውን ውጤት በየዓመቱም ሆነ የሦስት ዓመቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመገምገሙን የገለጹ ሲሆን በ2006፣ በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም የግምገማ ሪፖርት በተገኘ መረጃ አብዛኛዎቹ መ/ቤቶች የፕሮግራሞች እና የፕሮጀክቶች ዓላማዎች ተገምግመው በግብ ስኬት (outcome) ደረጃ የተደረሰባቸው ግቦች የማይገለጹ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፕሮግራሞችን የግብ ስኬት /outcome/ ለማየት በየአመቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ለመገምገም የመረጃ ችግር ስላለ እና ውጤቱን ለማየት እስከታችኛው የሥራው አካል መወረድ ስላለበት ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ የሦስት ዓመቱን ከ2004-2006 ዓ.ም. እና ከትራንስፎሜሽን ዕቅድ አንጻር መታየት የነበረበት ቢሆንም አለመገምገሙን በተጨማሪም መ/ቤቶች በጀት መጠይቅ ላይ እንጂ የፕሮግራሞች ውጤት የማይልኩ እና የአቅም ክፍተትም ስላለባቸው በዚህ ዓመት ከመርሐ ግብር ዝግጅት ጀምሮ ስልጠና ስለተሰጠ ወደፊት መሻሻሎች እንደሚኖሩ እንዲሁም ሥራውን ለመሥራት የመስሪያ ቤቱ አቅም ስለማይፈቅድ ለወደፊት በገለልተኛ አካል አማካሪ በመቅጠር ለመገምገም በክፍል ደረጃ እንደተነጋገሩበት ገልጸዋል፡፡

58. ጉዳዩን አስመልክቶ በመ/ቤታችን ለሚኒስትር መ/ቤቱ በተላከው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በተሰጠው መልስ የ2004-2006 ዓ.ም. የመጀመሪያው ሳይክል በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት የነበረው ለፕሮግራሞች፣ ለውጤቶች እና ለውጤት መለኪያዎች

አቀራረጽ በመሆኑ እንዲሁም የኘሮግራሞች የ3 ዓመት የግብ ስኬት ለማስቀመጥ የመነሻው (Baseline) መረጃ የሚፈለገውን ጥራት ጠብቆ የተዘጋጀ ባለመሆኑ እና የ2004-2006 የአፈፃፀም ሪፖርት እንዲያቀርቡ ከሚጠብቅባቸው መ/ቤቶች በአብዛኛው በግብ ስኬት ደረጃ አፈፃፀማቸውን ባለማቅረባቸው ግምገማ ለማድረግ ባለማስቻሉ ግምገማው ሊካሄድ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

59. የኘሮግራም በጀት ዋናው ዓላማ በጀትን ከውጤት ጋር ማስተሳሰር በመሆኑ የኘሮግራሞች ውጤታማነት አለመለካቱ ለየውጤቱ የተመደበው በጀት ያመጣውን ለውጥ ለማወቅ እየተደረገ ያለው ጥረት አነስተኛ በመሆኑ አሰራሩ የኘሮግራም በጀት መርህን ያልተከተለ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ለ. የኘሮግራም በጀት አላማዎችን ለማስፈጸም የተዘረጋው ሥርአት፣ ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

መ/ቤቶቹ ኘሮግራም በጀትን ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት መኖራቸውንና የኘሮግራም በጀት እና ውጤት ተኮር ዕቅድ ለማቀናጀት የተሰሩ ሥራዎችን በተመለከተ፤

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ አስፈጻሚ መ/ቤቶች የኘሮግራም በጀቱን ለመፈፀም የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል አደረጃጀት እና ግብዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

61. ሚኒስትር መ/ቤቱ የኘሮግራም በጀት እና ውጤት ተኮር ዕቅድና ሪፖርት ተመጋጋቢ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጠቅላላ ሥራውን ለመተግበር በመዋቅር የተፈቀደለት 47 የሰው ኃይል ቢሆንም አገልግሎት ላይ ያለው 20 /42 %/ የሰው ኃይል ብቻ መሆኑ፣ በተጨማሪም ክፍሉ ላሉት 165 ባለበጀት መ/ቤቶች ቀጣይና ተከታታይ የሆነ የመስክ ጉብኝትና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የተለየ ክፍል አለመኖሩና ሥራው በሌሎች ባለሙያዎች በተደራቢነት እየተሰራ የሚገኝ በመሆኑ የክትትልና የግምገማ ሥራው ለማከናወንና ከሥራው ስፋትና ጥልቀት አንጻር ያለው ሰው ኃይል ሥራው ለማስኬድ በቂ እንዳልሆነ በክፍሉ ባለሙያዎች በቃለ መጠይቅና ከሚኒስትር መ/ቤቱ በተገኙና በተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. በናሙና ከታዩ መ/ቤቶች የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ አደረጃጀት ያለው እና የፕሮግራም በጀት ዳይሬክቶሬት በሚል በዳይሬክተር ደረጃ የተዋቀረ፣ ኃላፊዎች በጀታቸውን እንዲከታተሉ በየክፍሉ የአይቤክስ ሥርዓት የተዘረጋ እና እንደ መሥሪያ ቤቱ ባህሪ የራሳቸው የፕሮግራም በጀት የአሰራር መመሪያ የአዘጋጁ ቢሆንም በተቀሩት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ራሱን የቻለ ክፍል የሌለውና በቡድን መሪ/ኬዝ ቲም/ የሚሰራ መሆኑ፣ የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የፕላኒንግ ፖሊሲ፣ የውጭ ግንኙነትና ክትትል ክፍል አንድ ቦታ ላይ መሆኑና በጀት ዝግጅቱም የሚከናወነው በዚህ ክፍል ሲሆን ያለው የሰው ኃይል ቁጥር ትንሽ በመሆኑ የተለያየ አገልግሎት እንደመስጠቱ ፕሮግራም በጀትን ለመተግበር አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፤ በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የሚሰለጥነው የሰው ኃይል በየጊዜው ስለሚለቅ ሥራውን በማንዋሉ መሰረት መሥራት እንዳልቻሉ የየመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

64. ዩኒቨርስቲዎችን በተመለከተ በአዳማ ዩኒቨርስቲ የፋይናንስ ግዥና አስተዳደር ዳይሮክቶሬት ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ዘርፍ ም/ፕሬዝዳንት ሲሆን ከእቅድ ክፍሉ ጋር ያለዉ ግንኙነት የጎንዮሽ በመሆኑና እያንዳንዱ ሥራ በክፍሉ ቢታቀድም በጀት ድልድሉ በፋይናንስ ክፍሉ መሰራቱ የክፍሎች ሪፖርት ለዕቅድ ክፍሉ ሲደርስ በጀት አጠቃቀሙና ዕቅድ አፈጻጸም ተመጋጋቢ መሆኑን ማረጋገጥ ላይ ክፍተት መፍጠሩ፣ በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ በአደረጃጀት ዕቅድና በጀት መምሪያው የተለያየ መሆኑና ክፍሎች ዕቅድን ከበጀት ጋር አስተሳስሮ ያለማምጣት፣ ለየተግባራቱ የተመደበውን በጀት ከፋይናንስ በማምጣት የሚያውቁ በመሆኑ አሰራር ላይ ክፍተት መፍጠሩን ችግሩን ለመፍታት አዲስ መዋቅር ተሰርቶ መጽደቁን፣ በዲላ ዩኒቨርስቲ በፊት በነበረው አደረጃጀት ኮሌጆች እየሰሩ ሲመጡ አመቺ ባለመሆኑ ሰፊ ክፍተቶች እንደነበሩና በጀት አጠቃቀማቸው በዕቅድ ክፍሉ ማወቅ እንደማይቻል፤ ለወደፊቱ ችግሩን ለመቅረፍ አዲስ አሠራር እንደተሰራና ተግባራዊ እንደሚሆን በዕቅድ ክፍሉ ሥር በጀት ክፍል ተከፍቶ ወደ ስራ ለመግባት በዝግጅት ላይ እንደሆኑና ለወደፊቱ የበጀት አናሊስ እንደሚኖራቸው የየዩኒቨርስቲው የዕቅድ ክፍል ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

65. በሌላ መልኩ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስትራቴጂክ ፕላኒንግ ዳይሬክቶሬት በውጤት ተኮር /BSC/ መሰረት እቅድ አቅዶ የአፈጻጸም ሪፖርት የሚያዘጋጅ፣ በጀትን በተመለከተ በክፍሉ የማያልፍና የፕሮግራም በጀትን ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑ፣ የመሠረተ ልማት ክፍሉ በራሱ የፕሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርት የሚያወጣና የበጀት መምሪያው የፋይናንሻል አፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ለብቻው የሚልክ ቢሆንም ሦስቱ ክፍል ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው ሲሆን ሁለቱ ክፍል የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን ከ2006-2008 ዓ.ም የማይልኩና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌላቸው በኦዲቱ ወቅት የየክፍሉ ኃላፊዎች ተናግረዋል፡፡

66. እንዲሁም የፕሮግራም በጀት እና ውጤት ተኮር ዕቅድን (BSC) ሊያቀናጅ የሚችል ጥናት ማጥናትን በተመለከተ ህዳር 2008 ዓ.ም በመ/ቤቱ በፕሮግራም በጀት እና በውጤት ተኮር አሰራር አንድነትና ልዩነት በሚል ተዘጋጅቶ ወደ ሲቪል ሰርቪስ መ/ቤት የተላከ ቢሆንም ሰነዱ ሊያቀናጅ በሚችል መልኩ ተጠናቆ ሥራው በመ/ቤቶች ላይ ወርዶ እየተሰራበት አለመሆኑ ከተዘጋጀው ሰነድና ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ችለናል፡፡

67. በናሙና በታዩት በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ከላይ በተገለጸው መሰረት አደራረጀቱ የተሻለ በመሆኑ በሪፖርት አዘገጃጀት ላይ ችግር ያልገጠማቸው ቢሆንም በተቀሩት መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀትና የውጤት ተኮር/BSC/ በአገር አቀፍ ደረጃ አለመቀናጀቱና ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ዝርዝር ተግባራት የማያይ በመሆኑ የተለየ ሪፖርት የሚዘጋጅና ለሚመለከታቸው የተለያዩ አካላት /ለምክር ቤት፣ ለሲቪል ሰርቪስ፣ ለብሔራዊ ፕላኒንግ ኮሚሽን…./ በቢ.ኤስ.ሲ መሠረት እንደሚልኩ፣ ከዕቅድ ጀምሮ እስከ አፈጻጸም የተለያየ ሪፖርት እንደሚዘጋጅና የተለያየ ፎርማት በመኖሩ በሥራ ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ በመሆኑ ለሪፖርቱ መዘግየትና ጥራት ማነስ አንዱ ምክንያት እንደሆነ የገለጹ ሲሆን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በዚህ ጉዳይ ባለበጀት መ/ቤቶች እንዲስተካከል የጠየቁ ቢሆንም ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና ሲቪል ሰርቪስ እየተነጋገሩበት እንደሆነ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመግለጹ ውጭ የተሰራ ሥራ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

68. በተጨማሪም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከ2008-20012 ዓ.ም. የስትራቴጂክ ዕቅድና የመ/ቤቶች ሪፖርት ግምገማ/የ2007 ዓ.ም./ በተገኘ መረጃ የፕሮግራም በጀት ከውጤት ተኮር ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ አንዳንድ መ/ቤቶች በፕሮግራም በጀት የጸደቁ ውጤቶችን ላይ ሳይሆን በውጤት ተኮር (BSC) ባስቀመጧቸው ዕቅዶች መሰረት ሪፖርት የሚልኩ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስትሩ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ እና ስለጉዳዩ በመ/ቤታችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተላከ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በተሰጠ መልስ የሰው ኃይል አደረጃጀትን በተመለከተ የብሔራዊ ፕላኒንግ ኮሚሽን ልክ እንደውስጥ ኦዲቱ የሁሉም መ/ቤቶች አደረጃጀት ላይ ከደሞዝ ጀምሮ ጥናት አድርጐ እንደጨረሰና ወደ ትግበራ ሊገባ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

70. ምንም እንኳን ብሔራዊ ፕላኒንግ ኮሚሽን የሰው ኃይል አደረጃጀትን በተመለከተ ጥናት ቢያደርግም ሚኒስትር መ/ቤቱ ፕሮግራም በጀትን ለመተግበር የሚያስችል መሆኑን ከአጥኚው አካል/የብሔራዊ ፕላኒንግ ኮሚሽን/ ጋር ሊነጋገርብትና አጽኖት እንዲሰጠው ሊያደርግ ይገባ ነበር፡፡

በመ/ቤቶች ከፕሮግራም ወደ ፕሮግራም የሚደረግ የበጀት ዝውውር አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያን መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤

71. በፕሮግራሞች ወይም በፕሮጀክቶች እና በመደበኛ ዋና ተግባራት መካከል የሚደረግ የበጀት ዝውውር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና በፋይናስ ደንብ እንዲሁም በፕሮግራም በጀት የበጀት ዝውውር አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ሊከናወን ይገባል፡፡

72. በፋይናንስ የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 10/1-ሐ ላይ አንድ የመንግሥት መ/ቤት የመደበኛና የካፒታል በጀት በሥራ ፕሮግራሙ መሠረት የማይጠቀምበት ሆኖ መገኘቱ ሲያረጋግጥ እጥረት ወዳለበት የመንግሥት መስሪያ ቤት ማዘዋወር ይችላል የሚልና ዝውውር የሚደረግ ቢሆንም መ/ቤቶች የያዙትን በጀት ያልተጠቀሙበትን ምክንያት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይጠየቅ፣ የመ/ቤቶች

የዕቅድ ክፍተት መኖሩን እና ለማይሰሩት ሥራ በጀት መያዛቸውን የሚያሳይ እንዲሁም በጀት የተያዘባቸው የፕሮግራሞች ውጤት ላይ የሚያመጣው ክፍተት የፕሮግራም በጀት መርህን /በጀትን ከውጤት ጋር ማስተሳሰር/ የሚጻረር ሲሆን ለማሳያ ያህል፤

73. በትምህርት ሚኒስቴር በ2006 በጀት ዓመት ከአፍሪካ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ከተያዘው በጀት ብር 27,355,650 /ሃያ ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ብር/ተቀንሶ ወደ ለከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት ብቃት ማጎልበት ፕሮጀክት ዝውውር የተደረገና 5,196,848 /አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ስምንት ብር/ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ተመላሽ የተደረገ ቢሆንም የአፍሪካ አቅም ግንባታ ሥራው አፈጻጸም ደካማ መሆኑ፣

74. በተመሳሳይ ለ2007 በጀት ዓመት ለአፍሪካ አቅም ግንባታ ኢንስቲትዩት ፕሮጀክት ግንባታ ብር 51,153,091 ሚሊዮን /ሃምሳ አንድ ሚሊዮን መቶ ሃምሳ ሦስት ሺ ዘጠና አንድ ብር/ለግንባታው አቅዶ የያዘ ቢሆንም ጨረታው ዘግይቶ ግንቦት መጨረሻ ወር ላይ በመውጣቱ ምክንያት በጀት ዓመቱ አለቀ በሚል ሃሳብ ለፕሮጀክቱ የተመደበውን ገንዘብ ወደ ሌላ ፕሮጀክት ዝውውር መደረጉና ይህም በተያዘው ፕሮግራም መሠረት ሥራዎች አለመከናወናቸውን ከውጤት አንጻር ለመመዘን የማያስችል ሲሆን ይህ ፕሮጀክት በ2008 በጀት ዓመትም አፈጻጸሙ እጅግ አዝጋሚና 0.3% መሆኑ፤

75. እንዲሁም በትምህርት ሚኒስቴር በ2007 በጀት ዓመት በስራ አመራር ፕሮግራም ሥር ለሚከናወኑ ተግባራት 108,771,150 /መቶ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ አንድ መቶ ሃምሳ ብር/የተያዘ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ ሊሰሩ የታቀዱትን ተግባራት በመሰረዛቸው ምክንያት ብር 19,253,357/አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ ሶስት መቶ ሀምሳ ሰባት ብር/ ወደ ሌላ ፕሮግራም ዝውውር መፈጸሙና ብር 20,498,636 /ሃያ ሚሊዮን ብር አራት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር/በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ፈሰስ መደረጉ፣

76. በተጨማሪም ሰኔ 13 ቀን 2008 ዓ.ም. ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከተቀናጀ የኢሚግሬሽን ቁጥጥር ኢንፎርሜሽን ፕሮጀክት ከተያዘው በጀት በጠቅላላ ብር 27,907,119.82 /ሃያ ሰባት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባት ሺ አንድ መቶ አሥራ

ዘጠኝ ብር ከሰማንያ ሁለት ሳንቲም/ለዲላ ዩኒቨርስቲ ለመኖሪያ ሕንጻዎች ግንባታ፣ ለመሠረተ ልማት ግንባታ ዝውውር የተደረገ ቢሆንም ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ለምን ፕሮጀክቱ እንዳልተፈጸመ የተገለጸ ማብራሪያ አለመኖሩ፣ በተመሳሳይ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ከዲጂታል ቴሌቪዥን ስርጭት ፕሮጀክት ከተያዘው ብር 30,742,788.75 ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለፈርኒቸር፣ ለቁሳቁስና ተገጣጣሚ ዕቃዎች መግዣ በ15/9/08 መዞሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

77. በዚሁ መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 10/3-ለ ላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ በዝርዝር በመሙላት በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ፊርማ በማረጋገጥ ከበቂ ማብራሪያና ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር መያያዙን መረጋገጥ አለበት ቢልም ከመጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ ጋር ማብራሪያና ደጋፊ ማስረጃ አለመያያዙን ከተከለሱ የመ/ቤቶች ማህደር ለማየት የተቻለ ሲሆን ከአንድ ፕሮግራም ወደ ሌላ ፕሮግራም የበጀት ዝውውር በተለያዩ ወጪ መደቦች መካከል በስፋት የሚያደርጉ መ/ቤቶች በመኖራቸው በውጤቶች፣ በዋና ዋና መደበኛ ተግባራት ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ በአግባቡ አለመታየቱ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ይህ አሰራር በፕሮግራም ወይም በውጤት ላይ የተመሰረተ አሰራር አለመኖሩን አመላካች ነው፡፡ ለአብነት ያህል፡-

78. በፕሮግራም በጀት መሰረት የተፈቀደው በጀት ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ ሳይውል ዝውውር የሚከናወን ሲሆን በኦዲቱ በታዩት በዲላ በጀት በጸደቀ በ23ተኛው ቀን ማለትም በ23/11/2007 ከበላይ አመራር ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት፣ ከመማር ማስተማር እንዲሁም ከምርምርና ስርፀት ጽ/ቤት ለፕላንት ማሽነሪ መሣሪያዎች መግዣ በጠቅላላው ብር 82,906,605/ሰማንያ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስድስት ሺህ ከስድስት መቶ አምስት ብር/፣ በትምህርት ሚኒስቴር በ17/12/2008 ዓ.ም. ከመኖሪያ ሕንፃዎች ግንባታ ወደ ኮንትራት ሠራተኞች አበል እና ለጭነትና በጀት ላልተመደበለት የወጪ መደብ፣ ለኮንትራት ሰራተኞች አበል፣ ለኪራይ ብር 4,417,047.00/አራት ሚሊዮን አራት መቶ አሥራ ሰባት ሺህ ከአርባ ሰባት/፣ የውሃ፣ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር በነሐሴ 24 ቀን 2008 ዓ.ም. ከመሰረተ ልማት ግንባታ መኖሪያ ያልሆኑ ህንጻዎች ግንባታ ብር 56,028,000.00 /ሃምሳ ስድስት

ሚሊዮን ሃያ ስምንት ሺህ ብር/ ዝውውር መደረጉን ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

79. እንዲሁም በአመቱ መጨረሻ የበጀት ዓመቱ ማለቂያ አንድ ወር ሲቀረው የበጀት ዝውውር ያለ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት ከታዩት በትምህርት ሚኒስቴር በ2008 በጀት ዓመት ከሰኔ 13/08-27/08 ድረስ ከቋሚ ሠራተኞች ደመወዝ፣ ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልገሎት፣ ከሕንፃ ቁሳቁስ እና ከተገጣጣሚዎች መግዣ፣ ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ፣ ከደን እና ለባህር ግብዓቶች ክፍያ፣ ወደ ለደንብ ልብስ፣ ለፍራሽና አልጋ ልብስ፣ ለሕንፃ ለቁሳቁስ እና ለተገጣጣሚዎች፣ ለአላቂና የቢሮ ዕቃዎች መግዣ፣ ለተሽከርካሪ እና ለሌሎች መጓጓዣዎች ዕድሳት እና ጥገና፣ ለተለያዩ ክፍያዎች ለመስተንግዶ አጠቃላይ ብር 30,235,261.45 /ሰላሳ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/እንዲሁም በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ከግንቦት 15 እስከ ሰኔ 29 ቀን ባሉት የተለያዩ ቀናት ውስጥ በ2008 ዓ.ም. ብር 28,116,891/ሃያ ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ አሥራ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና አንድ ብር/፣ በ2007 በጀት ዓመት 79,114,843/ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ አሥራ አራት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሦስት ብር/፣ በ2006 በጀት ዓመት 2,263,205.57 /ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ አምስት ብር ከሃምሳ ሰባት ሳንቲም/ የበጀት ዝውውር ያደረጉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ዝውውሩ የተደረገው ከደሞዝና የሥራ ማስኬጃ መጠባበቂያ ለደንብ ልብስ/ሰኔ 29/፣ ለቀን ሰራተኛ ክፍያ፣ ለጡረታ መዋጮ ለተቋሞችና ድርጅቶች እርዳታ፣ መዋጮና ድጎማ እና ለቋሚ ሰራተኞች ደሞዝና መዋጮ ዝውውር መደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

80. ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ከመስከረም ጀምሮ ዓመቱን ሙሉ በጀት ዝውውር ያደረገ ሲሆን በ27/10/2008 ዓ.ም. ከደመወዝና የሥራ ማስኬጃ መጠባበቂ ለመኖሪያ ሕንፃዎች፣ መኖሪያ ላልሆኑ ሕንጻ ግንባታዎችና ለቅድመ ግንባታ ሥራዎች ብር 212,397,647.00 /ሁለት መቶ አሥራ ሁለት ሚሊዮን ሦስት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ ስድስት መቶ አርባ ሰባት ብር ዝውውር የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም በ28/10/2008 ዓ.ም. ከከተማ መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ለልዩ ልዩ ወጪ፣ ከሥራ አመራር አስተዳደር ኘሮግራም ለትርፍ ሰዓት ክፍያ፣

ለስልክ አገልግሎት፣ ለስልጠናና ለቋሚ ሰራተኞች የጡረታ መዋጮ፣ ከሥራ አመራርና አስተዳደር ኘሮግራም ለልዩ ልዩ ክፍያዎችና ለትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 4,748,424 /አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሃያ አራት ብር/ በጠቅላላው ብር 217,146,071 /ሁለት መቶ አሥራ ሰባት ሚሊዮን መቶ አርባ ስድስት ሰባ አንድ ብር/ ዝውውር የተደረገ መሆኑ፣ በተመሳሳይ በግንቦት ወር ብር 46,240,812.9/አርባ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሺህ ስምንት መቶ አሥራ ሁለት ብር ከዘጠና ሳንቲም/፣ በመጋቢት ወር ብር 126,337,173.68 /መቶ ሃያ ስድስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ መቶ ሰባ ሦስት ከስልሳ ስምንት ሳንቲም/የተደረገ ሲሆን በየካቲት፣ በጥቅምት፣ በጥር፣ በታህሳስ እና ህዳር ወሮችም ዝውውሩ በመኖሩ በኘሮግራሙ መሰረት እየሰሩ አለመሆኑን ለማየት ችለናል፡፡

81. በተመሳሳይ ውሃ፣ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር አንድ ወር ውስጥ ብዙ ጊዜ ዝውውር የተደረገ ሲሆን ለምሳሌ በ2008 ዓ.ም በሰኔ ወር 31 ጊዜ በተለያየ ቅጽ ብር 156,071,653.85 /መቶ ሃምሳ ስድስት ሚሊዮን ሰባ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ሦስት ብር ከሰማንያ አምስት ሳንቲም/እና በሰኔ ወር 2008 ዓ.ም. 28 ጊዜ በተለያየ ቅጽ ብር 162,077,938.62 /መቶ ስልሳ ሁለት ሚሊዮን ሰባ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከስላሳ ሁለት ሳንቲም/በጠቅላላ ብር 318,149,592.47 /ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሚሊዮን መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/በሁለት ወር ውስጥ ተደርጓል፡፡

82. እንዲሁም ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአንድ ወር /በሰኔ/ 27 ጊዜ በተለያየ ቅጽ በጠቅላላ ብር 98,118,440.19 /ዘጠና ስምንት ሚሊዮን መቶ አሥራ ስምንት ሺህ አርባ አራት ከአሥራ ዘጠኝ ሳንቲም/ዝውውር የተደረገ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ወደ ለጭነት፣ ለደንብ ልብስ፣ ለፍራሽ እና ለአልጋ ልብስ መግዣ፣ ከምግብና ከተለያዩ መጣሪያዎች መግዣ ወደ አላቂ እቃዎች መግዣ፣ ከቢሮ ከቋሚ ሠራተኛ ደሞዝ ወደ ተሸከርካሪ እና ለሌሎች ግዥዎች ዕድሳት እና ጥገና የመሳሳሉት ላይ ዝውውር ተደርጓል፡፡ እነዚህ ዝውውሮች ከላይ ባየነው መመሪያ መሰረት ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በስተቀር ደጋፊ ሰነድ ወይም ማብራሪያ አብሮ አልተያያዘም፡፡

83. በኦዲቱ በታዩ በሁሉም መ/ቤቶች ለበጀት ዝውውር መብዛት ምክንያቶች ሲገልጹ በየፕሮግራሙ የሚዘጋጀው የፕሮግራም በጀት ጥያቄ በኃላፊዎች ዘንድ በቂ ትኩረት ተሰጥቶትና ውይይት ተደርጎበት ስለማይዘጋጅ እና በሥራው ላይ በቂ ገንዛቤ በሌላቸው ባለሙያዎች የበጀት ዕቅድ እንዲዘጋጅ ስለሚደረግ ከማስፈጸም አቅም በላይ ወይም በታች በጀት የሚያዝ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን በከተማ ልማት በተገኘ መረጃ የፕሮግራም በጀት መሠረት ያደረገበት የፊዚካል ዕቅድ በየጊዜው የሚከለስ መሆኑና የተፈቀደ በጀት ከፊዚካል መርሐ ግብር ጋር የተናበበ ያለመሆኑ ወይም የበጀትና የዕቅድ አለመቀናጀት እንዲሁም የበጀት ዕቅድ በሥራ አመራር የሚገመገም ባለመሆኑ በየመምሪያው ያለውን ችግር በሚገባ ለማየት አለማስቻሉ፣

84. በተመሳሳይ በትምህርት ሚኒስቴር የፕሮግራም ባለቤት ኃላፊዎች በቂ የሆነ የፕሮግራም በጀት አዘገጃጀት ግንዛቤ አለመኖርና በጀትን ለተመደበለት ውጤት አለመጠቀም፣ አንዳንድ ጊዜ የማያስፈልግ በጀትን መመደብ እንዲሁም በጀትን በማቀድና አጠቃቀሙን በወቅቱ ባለመከታተል የተነሳ በርካታ የበጀት ዝውውር እንዳለ ነገር ግን በዓመቱ መጨረሻ የሚመለሱ በጀቶች መኖራቸው እና በዓመቱ የተሰሩ እና ያልተሰሩ ሥራዎች ሳይታወቁ አስቀድሞ /ጥር 15/ የሚቀጥለው ዓመት ዕቅድ የሚታቀድ መሆኑ በፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑ፣

85. በሌላ መልኩ በውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴርና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስራ ክፍሎቹ ከፋይናንስ ጋር ተነጋግረው ዕቅድ ክፍሉ ሳይውቅ ዝውውር እንደሚያደረጉና ገንዘብ ሚኒስቴርም የዝውውሩን አስፈላጊነት ሳያረጋግጥ እንደሚፈቅድ፣ ከዕቅድ ጀምሮ እስከ ውጤቱ ድረስ ያለው ግምገማ ክፍተት መኖሩና የፕሮግራሙ አፈጻጸሙን የሚመለከተው አካል ባለመኖሩ ፕሮግራም በጀት በመ/ቤታችን አለ ለማለት አያስችልም ሲሉ ገልጸዋል፡፡ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ፣ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር እና ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ኃላፊዎች በዓመቱ መጨረሻ ተደጋጋሚ የበጀት ዝውውር መኖሩ የፕሮግራም በጀት እየተተገበረ አይደለም ለማለት የሚያስደፍር መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

86. በተጨማሪም በበጀት አስተዳደር ወቅት ከአንድ ፕሮግራም ወደ ሌላ ፕሮግራም የበጀት ዝውውር በተለያዩ ወጪ መደቦች መካከል በስፋት መደረጉ በውጤቶች፣ በዋና ዋና መደበኛ ተግባራትና ካፒታል በጀት ፕሮጀክቶች ግቦች ላይ ተግዳሮቶች እና ተፅዕኖዎች ሊያሳድር ስለሚችል ተጽዕኖ በአንዳንድ መ/ቤቶች እንደማይገለጽ ነገር ግን መገለጽ እንዳለበት የመ/ቤቶች የአፈጻጸም ሪፖርት ግምገማ ለማወቅ ችለናል፡፡

87. ስለ ጉዳዩ በገንዘብ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የበጀት ዝውውር መብዛት ምክንያት የዕቅድ አስተቃቀድ ችግር መሆኑና መ/ቤቶች ሥራ አለመሥራታቸው እንደ ጥሩ ባይቆጥሩትም አንድ መ/ቤት ሥራ አለመስራቱን ሲያረጋግጡ ሌላው መ/ቤት እንዲሰራበት ዝውውር እንደሚፈቅዱ በነሱ በኩል ፕሮግራሞች ላይ ጫና እንዳይፈጥር ዝውውር የሚደረግበት ፕሮግራም ባለቤቶች የዝውውር ፎርሙ ላይ እንዲፈርሙ እንደሚደረግ ነገር ግን በደንብ ያልገባቸው መ/ቤቶች ስላሉ ከላይ የመ/ቤቱ ኃላፊ ካዘዘ የመፍቀድ ሁኔታ መኖሩ የበላይ ኃላፊውም ቢሆን የፕሮግራም ኃላፊውን ፍቃድ ሊጠይቅ እንደሚገባ በተጨማሪም በደብዳቤ ማብራሪያ እንዲገልጹ የሚያደርጉ ቢሆንም በትክክል ምክንያቱን የማይገልጹ መ/ቤቶች መኖራቸውን አስረድተዋል፡፡

88. ስለጉዳዩ በመ/ቤታችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተላከ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በተሰጠ መልስ ላይ የበጀት ዝውውርን በተመለከተ የበጀት ዝውውር መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ቢሆንም የሚደረጉ የበጀት ዝውውሮች እቅድና ውጤትን መሰረት ያደረጉ እና የፊሲካል ዲሲፒሊን ጠብቀው እንዲሰሩ ለአስፈፃሚ መ/ቤቶች አስፈላጊው ድጋፍ፣ ክትትልና ስልጠና መሰጠቱን እንዲሁም አሁን ባለው አሰራር ተራፊ በጀት የሆነበት ምክንያት በቃልና በደብዳቤ እንዲያሳውቁ እየተደረገ ያለ ሲሆን ወደፊት ግን ሁሉም መ/ቤቶች በደብዳቤ እንዲያሳውቁ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

89. በመሆኑም ከአንድ ፕሮግራም ወደ ሌላ ፕሮግራም የሚደረግ የበጀት ዝውውር ትኩረት ተሰጥቶት ዝውውር የሚደረግበትን ምክንያት ማብራሪያ እንዲያቀርቡ በማድረግ የፕሮግራም ውጤቶች ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ጫና አለመታየቱ

የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል በመሆኑ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>መ/ቤቶች ሥርዓተ ፆታን በፕሮግራሞቻቸውና በፕሮጀክቶቻቸው ማካተታቸውን በተመለከተ፤</u>

90. መ/ቤቶች ሥርዓተ ፆታን በፕሮግራማቸውና በፕሮጀክቶቻቸው በማካተት፣ በበጀት ውስጥ ጎልቶ እንዲታይና ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ሊያደርጉ ይገባል፡፡

91. ይሁን እንጂ ሥርዓተ-ፆታን በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት ተሰጥቶት የማይገመገምና በፕሮግራሞቻቸውና በፕሮጀክቶቻቸው ላይ በዕቅድና በበጀት አካተው የሚሰሩ መ/ቤቶች ጥቂት መሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

92. በ2006ና በ2007 በጀት ዓመት ስርዓተ ፆታን በዕቅዳቸውና በአፈጻጸም ሪፖርታቸው ላይ አካተው የሰሩ መ/ቤቶች ብዛት ከ155 የመንግሥት መ/ቤቶች 57 ብቻ /37 በመቶ/ መሆናቸው፣ በ2008 በጀት ዓመት የመ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት ዝርዝር ዕቅድ ላይ ሁሉም መ/ቤቶች ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርን ጨምሮ ያላካተቱ መሆኑ፤ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ክፍልም ከ2006-2008 በጀት ዓመት ከሥርዓተ ጾታ አንጻር ግምገማው ያልተደረገ መሆኑ ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በናሙና በታዩ ባለበጀት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች በ2008 ዓ.ም. ከውሃ፣ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር በስተቀር በየፕሮግራሞቻቸውና ፕሮጀክቶቻቸው የተፈጸሙ ሥራዎች በአፈጻጸም ሪፖርት ላይ አለመገለጹ ከየመ/ቤቶቹ ከተሰበሰቡ እና ከተከለሱ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

93. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስትሩ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በክፍላቸው ብዙ እንዳልተሄደበት ነገር ግን ዓላማ/ውጤት ሲቀርጹ ካሉት መስፈርቶች አንዱ ሥረዓተ ጾታ መሆኑና ስልጠና ላይ ይህን ለማሳወቅ ግማሽ ቀን እንደሚሰጠው፣ በየክፍሉ ፕሮግራምና ፕሮጀክት ሲቀረጽ የሴቶችን ተጠቃሚነት እንዲታይ እንጂ ለብቻ እንዲታቀድ ባይፈለግም መ/ቤቶች ላይ የጠራ ግንዛቤ እንደሌለና እያንዳንዱ መ/ቤት በጥልቀት ማሳየት እንዳልቻሉ፣ የሥራው ባለቤት /የህጻናት፣ ወጣቶችና የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር/ ያለው በመሆኑ ገንዘብና ኢኮኖሚ

ትብብር ሚኒስቴር ለብቻው መሥራት እንደሌለበትና በየመ/ቤቱ ያሉት የሥርዓተ ጾታ ዳይክቶሬቶችም በጀት ሲዘጋጅ ማየት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

94. የሚኒስቴር ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የራሱን ድርሻ ለመወጣት በማንዋሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት የመ/ቤቶች አፈጻጸም ከሥርዓተ ጾታ አንጻር ግምገማ አለማድረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሚኒስትር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀትን በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡

95. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀትን በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም.ጀምሮ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

96. የፕሮግራም በጀትን ወደ ክልሎች ለማውረድ እንዲቻል በፕሮግራም በጀት ቅድመ ዝግጅትና አተገባበር ላይ ተከታታይ ሥልጠናና ድጋፍ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

97. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ፕሮግራም በጀት ክልሎች ላይ እየተሰራበት አለመሆኑን እንዲሁም በፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች በተወሰኑ መ/ቤቶች ላይ ሙከራ ወይም ፓይለት ፕሮጀክት ከተሰራ በኋላ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ በሁሉም መ/ቤት እንዲተገበር ማንዋል ተዘጋጅቶ የተሰራጨ ቢሆንም በማንዋሉ መሰረት እየተሰራ አለመሆኑና ሚኒስቴር መ/ቤቱም በማኑዋሉ መሰረት የግምገማ ሥራው እየሰራ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

98. ክልሎችን በተመለከተ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ተጠይቀው ሲመልሱ ለኦሮሚያ፣ ለደቡብ እና ለአዲስ አበባ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮዎች ሥልጠና የተሰጠ ቢሆንም ተግባራዊ እንዳልሆነ የገለጹ ሲሆን በኦዲቱ በታዩት በደቡብ ክልል ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለአራት መ/ቤቶች ሥልጠናው የተሰጠና ወደ ፕሮግራም በጀት ለመግባት ቅድመ ዝግጅቱ ላይ መሆናቸው፣ የክልሉ የመካከለኛ ጊዜ ከ2009-2011 በጀት የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ ሰነድ የተዘጋጀ ቢሆንም የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ክልሎችን ወደ ፕሮግራም በጀት እንዲገቡ ለማድረግ ያለው ድጋፍና ክትትል ማለትም በክልሎች

ጥያቄው ካልቀረበ በስተቀር ኃላፊነቱን ወስዶ እንዲወርድ የሚያደርገው ጥረት አነስተኛ መሆኑ የሚመለከታቸው ኃላፊ ገልጸዋል፡፡

99. በተመሳሳይ በኦሮሚያ ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በገንዘብና ኢኮኖሚት ትብብር ሚኒስቴር ተጠርተው ወደ ኘሮግራም በጀት እንዲገቡ ከመነገሩና ለግማሽ ቀን ኦረንቴሽን ከመሰጠቱ በስተቀር በኘሮግራም በጀት በተመለከተ ከሚኒስትር መ/ቤቱ ጋር ግንኙነት እንደሌላቸው፤ ኘሮግራሙን ለመጀመር የሚያስችል ስልጠናም እንዳላገኙ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዮን በባለቤትነት እንደመያዙ የሙያ ድጋፍ በማድረግ ወደ ሥራ እንዲገባ ቢያደርግ ጥሩ ነው ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ሥራው ሴክተር ላይ የሚሰራ እንደመሆኑ የክልል ኃላፊዎች ሥራውን መቀበል ስላለባቸው አስፈላጊው ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ እንዲኖራቸው መደረግ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

100. በሌላ መልኩ ኘሮግራም በፌዴራል ደረጃ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በየኘሮግራሙ የሚዘጋጀው የኘሮግራም በጀት ጥያቄ በኃላፊዎች ዘንድ በቂ ትኩረት ተሰጥቶትና ውይይት ተደርጎበት ስለማይዘጋጅ፣ በሥራው ላይ በቂ ግንዛቤ በሌላቸው ባለሙያዎች የበጀት ዕቅድ እንዲዘጋጅ ስለሚደረግ ከማስፈጸም አቅም በላይ ወይም በታች በጀት የሚያዝ መሆኑ፣ የኘሮግራም በጀት መሠረት ያደረገበት የፊዚካል ዕቅድ በየጊዜው የሚከለስ መሆኑና የተፈቀደ በጀት ከፊዚካል መርሐ ግብር ጋር የተናበበ ያለመሆኑ ወይም የበጀትና የዕቅድ አለመቀናጀት ለበጀት አፈጻጸም አነስኛነት ምክንያት መሆኑ እንዲሁም የኘሮግራም በጀት ጥያቄ እና የፊዚካል ዕቅድ የሚዘጋጅበት ወቅት የተለያየ ስለሆነ በኘሮግራም በጀት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ እና የኘሮግራም በጀት አሰራሩን ሙሉ ለሙሉ እየተተገበረ ነው ለማለት እንደማያስችል በከተማ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ የበጀት አፈጻጸምን በተመለከተ በተጠና ጥናት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በትምህርት ሚኒስቴር የየክፍሉ ኃላፊዎች ወይም ከየክፍሉ የሚወከሉ ተወካዩች ስልጠና ስላላገኙ ኘሮግራም በጀትን በተመለከተ የአቅም ክፍተት መኖሩንና የበጀት ዝውውር የሚበዛ በመሆኑ በትክክል ኘሮግራም በጀት እየተተገበረ ነው ለማለት የሚያስችል አለመሆኑ፣

101. በተጨማሪም ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፕሮግራም በጀቱ እየተሰራ ያለው በፖሊሲና በፕላን ዳይሬክቶሬት ሥራ በኬዝ ቲም አስተባባሪ መሆኑና የፕሮግራም ኃላፊዎች ስለ ፕሮግራም በጀት ግንዛቤ የሌላቸውና አፈጻጸማቸውን ሪፖርት ሲያደርጉ በዝርዝር /by Narrative/ እንደሚልኩና ክፍላቸው በራሱ ግምት በመቶኛ ቀይሮ የሚልክ መሆኑ እንዲሁም በዕርዳታ የሚመጣ ገንዘብ አብረው ስለሚልኩ ከፍተኛ ችግር በመፍጠሩ ሙሉ ለሙሉ ወደ ፕሮግራም በጀት ገብተናል ለማለት እንደሚቸገሩ የየመ/ቤቱ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

102. የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር በዋና ዋና ጉዳዮች መሠረት ያደረገ ሥልጠና ስለማይሰጥ እንዲሁም በየዓመቱ የሚሰጠው ሥልጠና ፕሮግራም በጀትን ለማስፈጸም በቂ ባለመሆኑ ከዕቅድ አስተቃቀድ ጀምሮ ክፍተት መኖሩና የበጀት ምደባው በራሱ ውጤትን መሰረት ያደረገ እንዳልሆነና ውጤቶች ትኩረት ተደርጐ እየታዩ አለመሆናቸው፣ የፕሮግራሙን አፈጻጸም በአግባቡ እሚመለከተው አካል ባለመኖሩ ፕሮግራም በጀት በወረቀት/በማንዋሉ ላይ/ ያለውን ያህል በተግባር አለ ለማለት አያስችልም ሲሉ የሚመለከታቸው ኃላፊ ገልጸዋል፡፡

103. በሌላ መልኩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሮግራም በጀት የማይሰራበትና ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራባት ያለው ውጤት ተኮር / BSC/ መሆኑን እንዲሁም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር ፕሮግራም በጀት አስመልክቶ ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው ሲሆን የፕሮግም በጀት ዕቅዱ እና የበጀት ድልድሉ የሚሰራው የስትራቴጂክ ፕላኒንግ ዳይሬክቶሬት ሰብሳቢ እና የበጀት መምሪያ ምክትል ሰብሳቢ የሆኑበት ኮሚቴ በማቋቋም ሲሆን ኮሚቴው ሥራው ሲያልቅ የሚፈርስ፣ የፋይናንሻ አፈጻጸም ሪፖርት ብቻ በበጀት መምሪያው ተዘጋጅቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርብ መሆኑን ከየክፍሉ ኃላፊዎች ከቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

104. በተቀሩት ሦስቱ ዩኒቨርስቲዎች ፕሮግራሙን የሚተገብሩና የሚያቅዱ አካላት ጋር ሥልጠና ባለመሰጠቱ ተግባራቱን ከበጀት ጋር አጣጥሞ ወደ ዕቅድ ክፍሉ ለማምጣት የአቅም ውስንነት መኖሩና የኦፕሬሽናል ዕቅድ ከበጀት ጋር ተሳስሮ እየተሰራ አለመሆኑ እንዲሁም ከመማር ማስተማሩ ጋር በሚፈጠሩ ችግሮች ላይ እንጂ የፕሮግራሞች የበጀት ውጤት ላይ ትኩረት አለመስጠት/በጀቱን በዕቅድና

በመመሪያ መሰረት አለማስኬድ/፣ ፕሮግራም በጀት አሰራር ማገዝ የሚያስችል የቴክኖሎጂ አሰራር አለመኖር በተጨማሪም በአዳማ ዩኒቨርስቲ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ከቁጥር አንጻር በመቶ የተሰጠውን እንጂ ውጤት ባለመለካቱ ምክንያት በጀቱን ወደ ውጤት ለማድረስ ብዙ መሠራት እንዳለበት ኃላፊዎቹ ለኦዲት ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

105. አንዳንድ መ/ቤቶች በፕሮግራማቸው የያዙትን የፕሮግራም ውጤቶች ለማሳካት ርብርብ የሚያደርጉ ቢሆንም ለፋይናንስ አፈጻጸማቸው ግን ተገቢውን ክትትል በማድረግ በኩል ከፍተኛ የሆነ ውስንነት መኖሩ ወይም ወጪትን ከበጀት ጋር አስተሳስሮ ከመሄድ አንጻር ክፍተት መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በማንዋሉ መሰረት የግምገማ ሥራውን በአግባቡ እያካሄደ ካለመሆኑም በላይ ፕሮግራም በጀቱ ከተጀመረበት ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ ፕሮግራም በጀት በየመ/ቤቱ ያለበትን ደረጃ፣ ካለፈው አሰራር በትክክል ስለመወጣቱ እና ፕሮግራም በጀት በመተግበሩ የመጣውን ውጤት እስከ ኦዲቱ መጠናቀቂያ ድረስ አለመገምገሙን በቃለ-መጠይቅ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

106. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ፕሮግራም በጀቱ ያለበትን ደረጃና ያመጣውን ውጤት ለማወቅ የተሰራ ሥራ እንደሌለና በአሁኑ ወቅት ግን በሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅም ሥራውን ለመሥራት ስላልተቻለ አጽርሆት /TOR/ ተዘጋጅቶ በአለም ባንክ ጨረታ እንዲወጣና ኮንሰልታንት ሊቀጠር እንደታሰበ ገልጸዋል፡፡

107. በመ/ቤታችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተላከው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠው መልስ የፕሮግራም በጀቱ በመርህ ደረጃ የተዘጋጀውን የፕሮግራም በጀት ማኑዋል እና ዝርዝር የአዘገጃጀትና የአቀራረብ መመሪያ ተከትሎ እየተዘጋጀ ያለ፣ ጥራትን በተመለከተ ግን ወደፊት ሊስተካከል የሚችል መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ የገለጹ ሲሆን ፕሮግራም በጀቱ በክልሎች ተግባራዊ አለመሆኑን በተመለከተ የተሰጠ መልስ የለም፡፡

108. በመሆኑም ፕሮግራም በጀት በክልል ደረጃ አለመውረዱና በፌዴራል መ/ቤቶችም በማንዋል መሰረት አለመከናወኑ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር

ከማድረጉም በላይ ኘሮግራም በጀት ሙሉ ለሙሉ/በሚፈለገው ደረጃ እየተተገበረ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

ሐ. ሚኒስትር መ/ቤቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት እና ድጋፍ እንዲሁም ጠንካራ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ትስስር የፈጠረ መሆኑን በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች

<u>ተከታታይ ሥልጠና መስጠቱን በተመለከተ</u>፤

109. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሁሉም የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የኘሮግራም በጀትን አፈፃፀምን በሚመለከት ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

110. ይሁን እንጂ በናሙና በታዩት በሁሉም መ/ቤቶች ከ2006-2008 ዓ.ም. በየዓመቱ ለ3 ቀን ያህል ስልጠና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ቢሰጥም የሚሰጠው ስልጠና ፍላጎትን መሰረት አድርጐ፣ ክፍተቶች ለመሙላት ታስቦ እንዳልሆነ እንዲሁም ኘሮግራም በጀትን አስመልክቶ በዋና ዋና ጉዳዮችን መሠረት ያደረገ ካለመሆኑም በላይ ስልጠና የሚባል ሳይሆን ገለጻ /orientation/ እንደሆነ የየመሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎች የገለጹ ሲሆን በተጨማሪም በቂ ስልጠና ባለመሰጠቱና ስልጠናው የሚሰጠው ለዕቅድና በጀት ዝግጅት ክፍሎች እንጂ የኘሮግራሙ ባለቤት ለሆኑት ኃላፊዎች ባለመሆኑ ለኘሮግራም በጀት ትኩረት ያለመስጠት እና ከዕቅድ እስከ ሪፖርት ዝግጅት ድረስ በአሰራር ላይ ክፍተት መፍጠሩን የገለጹ ሲሆን በተጨማሪም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቢ.ኤስ.ሲ. መሰረት አድርጐ እንጂ ኘሮግራም በጀት ላይ እየተሰራበት አለመሆኑ፣ በዲላ ዩኒቨርስቲ ስልጠናው ለሁሉም መ/ቤት አንድ ላይ መሰጠቱና እንደሥራው ተመሳሳይነትና ውስብስብነት ተለይቶ መሰጠት እንዳለበት ለምሳሌ ዩኒቨርስቲዎች ለብቻ ቢሰጥ ሥልጠናው የሚሰጠው ሦስት ቀን በመሆኑና ከመ/ቤቱ ጋር የሚገናኙበት ብቸኛው መድረክ እንደመሆኑ መነሳት ያለባቸው ተመሳሳይ ችግሮች/ከተማሪዎች እና ከመማር ማስተማር ጋር በተያያዘ የሚመጡ ያልታሰቡ ሥራዎች/ ተለይተው እንደማይነሱና አመራሮች ትኩረት እንዲሰጡ የአሰልጣኞች ስልጠና መሰጠት እንዳለበት የገለጹ ሲሆን አዳማ ዩኒቨርስቲ ክፍተቱን ለመድፈን በጀት ይዘው ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያዎችን

ጠርተው ስልጠናው እንዲሰጥ እንዳደረጉ ኃላፊዎቹ ለኦዲት ቡድኑ በዝርዝር አስረድተዋል፡፡

111. ከዚህ በፊት የነበረው ስልጠና ከላይ በመ/ቤቶቹ የተገለጹ ችግሮች መኖራቸው ነገር ግን በዚህ ዓመት ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህን ተረድቶ የፕሮግራም ኃላፊዎች ስልጠናውን እንዲወስዱ የተደረገና የሚሰለጥነውም የሰው ኃይል ተጨምሮ 720 ሰው በተለያየ ጊዜ በመከፋፈል እየተሰጠ እንደሆነ በተጨማሪም እንደበፊቱ ገለጻ ሳይሆን የተግባር ስልጠና እንደተሰጠ ገልጸዋል፡፡

112. ስለጉዳዩ የሚኒስትር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ እና በመ/ቤታችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተላከው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠው መልስ የተሰጠው አስተያየት እስከ 2008 በጀት ዓመት ችግሩ የነበረ ቢሆንም በ2009 በጀት ዓመት ግን ስልጠናውን ተቋማዊ በማድረግ ተገቢው የስልጠና ማኑዋል፣ ማኑዋል እና ስላይድ /powerpoint/ በማዘጋጀት በ3 ዙር ለእያንዳንዱ ዙር ለ5 ተከታታይ ቀናት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ስልጠናው መሰጠቱ ይህም ወደፊት በበጀት ዝግጅትና በፕሮግራም በጀት ክትትልና ግምገማው ያለውን ችግር እንደሚፈታ ገልጸዋል፡፡

113. ስልጠናው ባለፉት አመታት በአግባቡ አለመሰጠቱ የመ/ቤቶች የበላይ አመራሮች ትኩረት እንዳይሰጡ የፕሮግራሙ ባለቤት የሆኑ ኃላፊዎች የአቅም ክፍተት በመፍጠሩ በማንዋሉ መሰረት ፕሮግራም በጀትን እንዳይተገብሩ አድርጓቸዋል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮግራም በጀት ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠሩን፣
በዕቅድ እና በበጀት ዝግጅት እንዲሁም በበጀት አስተዳደር ያጋጠሙ
<u>ችግሮችን ለመፍታት ከባለበጀት መ/ቤች ጋር ውይይት ማካሄዱን በተመለከተ</u>፤

114. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የባለበጀት መ/ቤቶች በፕሮግራም በጀት ዙሪያ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕ፣ በደብዳቤና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ ሊፈጥር ይገባል፡፡

115. በዕቅድ እና በበጀት ዝግጅት እንዲሁም በበጀት አስተዳደር ያጋጠሙ ችግሮችና ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮች በመለየት ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር በጋራ እና

አስፈላጊ ሲሆን በተናጠል ውይይት ለማካሄድ ሰነድ በማዘጋጀት ውይይት ሊያደርግ ይገባል፡፡

116. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በናሙና በታዩት /በዲላ፣ በሀዋሳ፣ በአዳማና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲዎችና በ6 ባለበጀት መስሪያ ቤቶች በሙሉ በአመት አንዴ በስልጠና ከሚነሳው አንድ አንድ ክፍተቶች ውጭ በዕቅድ እና በበጀት ዝግጅት እንዲሁም በበጀት አስተዳደር ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት የውይይት መድረክ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ የተጠሩበት ጊዜ እንደሌለ በተጨማሪም የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን አለመሰራቱን በቃለ-መጠይቅ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተለይ ዩኒቨርስቲዎች ላይ የግንዛቤ ሥራው ባለመሰራቱ ከፍተኛ አመራሮች ለኘሮግራም በጀቱ ትኩረት እንደማይሰጡና ለመማር ማስተማሩና ከመማር ማስተማሩ ጋር የሚገጥሙ ችግሮችን በአፋጣኝ ለመፍታት እንጂ በጀትን ከኘሮግራም ውጤት ጋር ማስተሳሰሩ ላይ ያሉ ክፍተቶች በሚፈለገው ደረጃ መቀረፍ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

117. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚገናኝበት የሕዝብ ክንፍ ያለ ቢሆንም የኘሮግራም በጀት የአሰራር ሥርዓት ላይ ተለይቶ አለመሆኑ እና የየመ/ቤቶቹ ከፍተኛ አመራሮች ሥራው የራሴ ነው የማለት ችግር እንዳለባቸው በማመን ችግሩን ለመፍታት ለወደፊቱ ኘሮግራም በጀትን ለይተው የግንዛቤ ሥራ እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በሚታዩ ክፍተቶች ላይ የውይይት መድረክ ባይዘጋጅም በበጀት ስሚ እና በስልጠና ጊዜ እንደሚነሳ ነገር ግን በቂ እንዳልነበርም አክለዋል፡፡

118. በመሆኑም የታዩት ክፍተቶች ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ያለውን የሥራ ግንኙነት የላላ መሆኑን የሚያሳይና በኘሮግራም በጀት አተገባበር ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በወቅቱ እርምት እንዳይወሰድ አድርጎታል፡፡

<u>በሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤</u>

119. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለጀት መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት አሰራር እና የመረጃ ልውውጥ የተቀላጠፈ እንዲሆን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት ሊጠቀም ይገባል፡፡

120. ፕሮግራም በጀት አሠራር መሠረት የሚከናወኑ ተግባራትን ወጪዎችን ከውጤቶች ጋር አስተሳስሮ መዝግቦ በመያዝ በኩል ሥራውን የሚያሳልጥ በሁሉም መ/ቤት ወጥ የሆነ የሶፍት-ዌር ባለመኖሩ በጀትን ከውጤት ጋር አስተሳስሮ ለመመዝገብ እና ሪፖርት ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን መፍጠሩ ከቃለ-መጠይቃና ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

121. ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በተገኘ መረጃ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በካፒታል በጀት ከሚሰራው ፕሮጀክት አንዱ ኢፍሚስ ሲሆን ከ2003-2007 ዓ.ም. የመ/ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ ከ2003-2004 የሶፍትዌሩን አሠራር ከመ/ቤቶች ፍላጎት አንጻር የማስተካከልና (Customization) የሙከራና የፍተሻ ሥራዎች ከተከናወኑ በኋላ በቀጣዮች ሦስት ዓመታት /ከ2005-2007/ወደ ሙሉ ትግበራ እንደሚሸጋገርና ከ1500 ያላነሱ ተቋማት (ወረዳዎች ጭምር) በሲስተሙ ተጠቃሚ እንደሚሆን የታቀደ ቢሆንም በ2008 በጀት ዓመት በ11 ባለበጀት መ/ቤቶች ላይ ብቻ የሙከራ ሥራ እየተሰራ እና ሌሎች መ/ቤቶች ግን አይቤክስ እየተጠቀሙ እንዲሁም የፕሮጀክቱ አፈጻጸም አነስተኛ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

122. በኦዲቱ ወቅት በታዩና ኢፍሚሱ ተግባራዊ በሆነባቸው በትምህርት ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴርና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኢፍሚሱ የፕሮግራም በጀት አሰራር ሥርዓት ይረዳል ተብሎ የታሰበ ቢሆንም እንደበፊቱ አሰራር በሂሣብ ኮድ የሚመዘገብና ወጪውን እንጂ ውጤቱን የማያሳይ፣ የፕሮግራም በጀት አሰራርን የማያግዝ መሆኑና ካለፈው አሰራር የወጣ አለመሆኑን የገለጹ ሲሆን በተጨማሪም እንደየመስሪያ ቤቱ ባህሪ ከመ/ቤቱ አሰራር ጋር ተጣጥሞ በሶፍትዌሩ ያልተካተተ መሆኑን ለምሳሌ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከ2007 ኦጋማሽ ጀምሮ ዋናው ግቢ የተጀመረ ቢሆንም ስርዓቱ ሲዘረጋ በስሩ ባሉ ክፍሎች እንዲሁም ሌሎች ዩኒቨርስቲና ኢንስቲትዮቶች አለመዘርጋቱና ወጥ የሆነ አሰራር አለመኖሩ፣ በተመሳሳይ በመንገዶች ባለሥልጣን የኢፍሚስ ስርዓቱ ፕሮጀክቶች ሲጀመሩ

ቅድመ ክፍያ ለመክፈል አስቸጋሪ መሆኑና ሌሎች ክፍያዎች/Retention payment/ ለመፈጸም የሚያስችል ሥርዓት የሌለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

123. እንዲሁም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በውሃ፣ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴርና በትምህርት ሚኒስቴር የሲስተም መቆራረጥ መኖሩን የገለጹ ሲሆን ከላይ በተጠቀሱት በሁሉም መ/ቤቶች ሶፍትዌሩን አስመልክቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰጠው ስልጠና በቂ ባለመሆኑ የባለሙያዎች የአቅም ክፍተት መኖሩ ገልጸዋል፡፡

124. በዲላ ዩኒቨርስቲ አይቤክስ እየተጠቀሙ ቢሆንም መጀመሪያ ፕሮግራሙ ሲቀረጽ በአራት ፕሮግራም መሆኑና ተግባራቱ እየበዙ ሲመጡ ለአሰራር እንዲመች በሚል በኤክሴል በመሥራታቸው በትክክል ከየትኛ ወጪ እንደሆነ ለማወቅ ክፍተት መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡

125. የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ዕቅዱ የብሔራዊ ፕላኒንግ ኮሚሽን መሆኑ ከላይ የተነሱ ችግሮች መኖራቸውና መ/ቤቶች በሚፈለጉት መልኩ አለመሆኑና ኢ.ፍሚሱ ከበጀት አጠቃቀም ውጭ የፕሮግራሞችን መለኪያና ውጤት የማያሳይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

126. ባለበጀት መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት ለመተግበር የሚያስችል ጠንካራ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ባለመኖሩ የፕሮግራም በጀት አሰራር ቀልጣፋ እንዳይሆን አድርጓል፡፡

ክፍል ሦስት

መደመደሚያ

127. **የባለበጀት መ/ቤቶች ያዘጋጁት የፕሮግራም በጀት በተያዘለት ጊዜና ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተልና ለመገምገም የተዘረጋው ሥርዓት ጠንካራ መሆኑን እንዲሁም የፕሮግራም በጀት በመተግበር የሚጠበቀው ውጤት መገኘቱን በተመለከተ፣**

- *በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ያለው የክትትል ሥራ በሪፖርት ሲሆን የተሟላ ሪፖርት የማይልኩ ማለትም ፋይናንሻል አፈጻጸምን ብቻ መሰረት ያደረገ ሪፖርት የሚልኩ /የፊዚካልና የፕሮጀክት አፈጻጸማቸውን የማይልኩ/ መ/ቤቶች መኖራቸው፣*

- *በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ መ/ቤቶች መርሐ ግብራቸውን እንዲልኩ የሚያደርግ ሲሆን ሪፖርታቸውንም ሆነ መርሐ ግብራቸውን በወቅቱ የማይልኩ፣ የሚልኩት የአፈፃፀም ሪፖርት መርሐ ግብራቸውን መሰረት ያላደረገ መ/ቤቶች መኖራቸው፣ ፊዚካልና ፋይናንሻል አጠቃቀማቸው ሰፊ ልዩነት ያለው እንዲሁም መርሐ ግብራቸውንና የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን በማንዋሉ መሰረት የማይልኩ መ/ቤቶች በመኖራቸው ያለው የክትትል ሥርዓት ላይ ክፍተት መፍጠሩ እና መ/ቤቶች በመርሐ ግብሩ መሰረት ስለማከናወናቸው ግምገማ ከተደረገ በኋላ ወጥነት ባለው መልኩ በጽሑፍና በጥልቀት ግብረ መልስ አለመሰጠቱ፣*

- *ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸምን አስመልክቶ ቅኝትና የመስክ ጉብኝት ለማድረግ* በ2008 *ዓ.ም. ብቻ ዝርዝር መርሐ ግብር ያዘጋጀ ሲሆን* በ2007 ከ155 *መ/ቤቶች በሦስት መ/ቤቶች ካሏቸው* 310 *ፕሮጀክቶች* 14ቱ /06%/ *ላይ ብቻ እንዲሁም* በ2008 *ዓ.ም.* ከ165 ባለበጀት *መ/ቤቶች* በ5ቱ 23 *ፕሮጀክቶች ለማየት መርሐ ግብር ተይዞ በሦስት* ባለበጀት *መ/ቤቶች ካላቸው* 304 *ፕሮጀክቶች* በ5ቱ /02%/ *ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ የመስክ ጉብኝት የተደረገ ሲሆን በሌሎች መ/ቤቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የመስክ ጉብኝት አለመደረጉ፣*

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የባለበጀት መ/ቤቶች የታለመ የውጤቶች ውጤታማነትም ሆነ ፕሮግራሞች ከግብ ስኬት አንጻር ያመጡት ውጤት ላይ የተሰራ ሥራ የለም፡፡ እንዲሁም መ/ቤቶች ከበፊቱ አሰራር /line item/ ወጥተው ፕሮግራም በጀቱ በፌዴራል መ/ቤቶች ከተጀመረ ጀምሮ የደረሰበትንና ያመጣውን ለውጥና ውጤት አልተገመገመም፡፡

128. የፕሮግራም በጀት አላማዎችን ለማስፈጸም የተዘረጋው ሥርአት፣ ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮግራም በጀትን ለማስተግበር የሚያስችል የሰው ኃይል የሌለው ማለትም በመዋቅር 47 የተፈቀደለት ቢሆንም ያለው የሰው ኃይል 20 የሰው ኃይል /42%/ ብቻ ሲሆን እንደባለበጀት መ/ቤቶች ብዛት/165/ ወጥና ቀጣይነት ያለው የመስክ ጉብኝትና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የተለየ ክፍል የሌለው መሆኑ፣ በናሙና በታዩ በሀዋሳ፣ በአዲስ አበባ፣ በዲላና በአዳማ ዩኒቨርስቲ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና በውሃ፣ የመስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የቢሮ አደረጃጀት እና ያለው የሰው ኃይል አቅም ፕሮግራም በጀት ለመትግበር በሚያስችል መልኩ አለመሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀት እና ውጤት ተኮር ዕቅዶችን ተመጋጋቢ ለማድረግ ጥናት ለማጥናት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህዳር 2008 ዓ.ም. በሁለቱ አንድነትና ልዩነት ላይ ሰነድ ያዘጋጀና ለሲቪል ሰርቪስ የላከ ቢሆንም ሥራው ሊቀናጅ በሚችል መልኩ ተጠናቆ ወደ መሥሪያ ቤቶች አልወረደም፡፡
- በናሙና በታዩ በሁሉም መ/ቤቶች የበጀት ዝውውር በዓመቱ መጀመሪያ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ሳይውል፣ በአመቱ መጨረሻ የዓመቱ ማለቂያ አንድ ወር ሲቀረውና ዓመቱን ሙሉ የበጀት ዝውውር የሚያደርጉ መ/ቤቶች መኖራቸውና ከአንዱ ፕሮግራም ወደ ሌላ ፕሮግራም ዝውውር ሲያደርጉ በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው ማብራሪያ እንዲያቀርቡ የማይደረግና ዝውውር በተደረገበት የፕሮግራሞች ውጤት ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ የማይገመገም መሆኑ፣ እንዲሁም ዝውውሩ ለአላቂ የቢሮ ዕቃዎች፣ ለፈርኒቸር፣

ለደንብ ልብስ፣ ለተሽከርካሪ እና ለሌሎች መጓጓዣዎች ዕድሳት እና ጥገና፣ ለጡረታ መዋጮ፣ ለተቋሞችና ድርጅቶች እርዳታ፣ መዋጮና ድጎማ ለተለያዩ ክፍያዎች ለመስተንግዶ፣ ለመሳሰሉት.... ጭምር መሆኑ፣ ዕቅድ ክፍሉ ሳይውቅ ከሒሳብ ክፍል ጋር በመነጋገር ዝውውር የሚያደርጉ መ/ቤቶች መኖራቸው፣

- በክልል ፕሮግራም በጀት እየተሰራበት አለመሆኑ፣ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማንዋል የተዘጋጀ ቢሆንም በማንዋሉ መሰረት እየተተገበረ አይደለም፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ከዕቅድ ጀምሮ እስከ አፈጻጸም ያለውን አሰራር በማንዋሉ መሰረት እየገመገመ ካለመሆኑም በላይ የፕሮግራሞች ከግብ ስኬት አንጻር ያመጡትንም ውጤትም ሆነ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ ፕሮግራም በጀት ያመጣውን ውጤት አይገመግምም፡፡
- ሥርዓተ ጾታን በተመለከተ ለብቻው በበጀት ላይ እንዲታይና መ/ቤቶች በሚቀርጹት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ የሴቶችን ተጠቃሚነት በዕቅድም ሆነ በአፈጻጸም ሪፖርት ላይ እንዲያሳዩ ማንዋሉ ቢያዝም በማንዋሉ መሰረት መ/ቤቶች ከውሃና፣ መስኖ ኤሌክትሪክ በስተቀር በሌሎቹ መ/ቤቶች በአፈጻጸም ሪፖርቶቻቸው ላይ አይገልጹም፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ትኩረት ሰጥቶ በሥርዓተ ጾታ አንጻር በጀትን፣ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞችን አይገመግምም፡፡

129. ሚኒስትር መ/ቤቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነትና እና ጠንካራ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ትስስር መኖሩን በተመለከተ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2006-2008 ዓ.ም. በየዓመቱ ለ3 ቀን የሚሰጠው ስልጠና ፍላጎትን መሰረት አድርጎ፣ ክፍተቶች ለመሙላት ታስቦ እንዳልሆነ እንዲሁም ፕሮግራም በጀትን አስመልክቶ በዋና ዋና ጉዳዮችን መሠረት ያደረገ ካለመሆኑም በላይ ገለጻ/orientation/ እንጂ ስልጠና የሚባል አለመሆኑ፣ በተጨማሪም ስልጠናው ለዕቅድና በጀት ዝግጅት ክፍሎች ብቻ እንጂ የፕሮግራሙ ባለቤት ለሆኑት ኃላፊዎች አለመሰጠቱ፣
- በአመት አንዴ በስልጠና ከሚነሳው አንድ አንድ ክፍተቶች ውጭ በዕቅድ እና በበጀት ዝግጅት እንዲሁም በበጀት አስተዳደር ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት የውይይት መድረክ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ አለማወቁ እና በሚኒስቴር

መ/ቤቱ ፕሮግራም በጀትን በተመለከተ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ላይ የሰራው ሥራ አለመኖሩ፣

- ፕሮግራም በጀት አሠራር መሠረት የሚከናወኑ ተግባራት ወጪዎችን ከውጤቶች ጋር አስተሳስሮ መዝግቦ በመያዝ በኩል ሥራውን የሚያሳልጥ በሁሉም መ/ቤት ወጥ የሆነ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አለመዘርጋቱ፣

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሐሳቦች

130. **የባለበጀት መ/ቤቶች ያዘጋጁት የፕሮግራም በጀት በተያዘለት ጊዜና ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተልና ለመገምገም የተዘረጋው ሥርዓት ጠንካራ መሆኑን እንዲሁም የፕሮግራም በጀት በመተግበር የሚጠበቀው ውጤት መገኘቱን በተመለከተ፣**

- *ሚኒስቴር መ/ቤቱ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር በሚፈለገው መልኩ በሰው ኃይል ሊያደራጅ፣ እራሱን የቻለ የክትትል ክፍል በማቋቋም ከሪፖርት በዘለለ መልኩ ቅኝት በማድረግ ሊከታተልና የካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ አስፈላጊውን የመስክ ጉብኝትም ሆነ ክትትል በማድረግ በጀቱ በትክክል ለተፈለገለት ዓላማ መዋሉንና በመርሐ ግብሩ መሰረት መሄዳቸውን በማየት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡*
- *ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በማያቀርቡ መ/ቤቶች ላይ አስገዳጅ የሆነ ሁኔታ በማስቀመጥ እንዲያቀርቡ ሊያደርግና የሪፖርት አቀራረብ ማንዋል ከመላክ ባሻገር በአቀራረቡ ላይ የታዩ ክፍተቶች ላይ ስልጠና ሊሰጥ፣ እንዲሁም በተላኩ ሪፖርቶች ላይ በወቅቱ የሪፖርት አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ የታዩ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስ በመስጠት በተሰጡ ሐሳቦች ላይ ማሻሻያ መደረጋቸው በቀጣይ ሪፖርት ላይ በማየት ሊያረጋግጥ እና የአፈጻጸም ግምገማው ከተጠያቂነት አንጻር እንደ በጀቱ በምክር ቤት እንዲታይ ሊያደረግ ይገባል፡፡*
- *ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለየፕሮግራሞች የተመደበው በጀት ምን ያህል ውጤታማ መሆኑን ለማወቅ የውጤቶች ውጤታማነትንና ፕሮግራሞችን ካስቀመጡት ግብ ስኬት አንጻር ያመጡትን ውጤት በመገምገም ለባለበጀት መ/ቤች ሊያሳውቅ እንዲሁም የፕሮግራም በጀት በፌዴራል ደረጃ የተደረሰበትንና ያመጣውን ውጤት በሌላ አካል ሊገመግም ይገባል፡፡*

131. **የፕሮግራም በጀት አላማዎችን ለማስፈጸም የተዘረጋው ሥርአት፣ ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤**

- *ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለውን የቢሮ አደረጃጀት በመፈተሽ ፕሮግራም በጀትን ለማስተግበር በሚያስችል መልኩ ሊዋቀርና በቂ የሆነ የየሰው ኃይል ሊመድብ፣ እንደሁም ባለበጀት መ/ቤቶች አስፈላጊው የቢሮ አደረጃጀት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡*
- *ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጀመረውን ሥራ እዳር ለማድረስ ከሲቪል ሰርቪስ ጋር በመነጋገር የፕሮግራም በጀትንና የውጤት ተኮር ዕቅዶችን ተመጋጋቢ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡*
- *ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ በሚፈቅደው ማለትም አንድ መ/ቤት የማይጠቀምበት ሆኖ ሲገኝ ወደ ሌላ መ/ቤት እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የልማት ተግባራት ለማከናወን በሚለው መሠረት ሊያከናውንና የፕሮግራም በጀትን ዓላማ መሰረት ባደረገ መልኩ የበጀት ዝውውሩ እንዲከናወን በሌላው ፕሮግራም ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ አስፈላጊውን ማብሪሪያ እንዲያቀርቡ በማድረግና የበጀት አጠቃቀምና ዕቅድ ላይ መ/ቤቶች ያለባቸውን ክፍተቶች ለመሙላት አስፈላጊውን ስልጠና በመስጠት የበጀት ዝውውሩ በአግባቡ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በዓመቱ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ያሉትን የበጀት ዝውውሮች ለማስቀረት የበጀት ዝውውሮችን የጊዜ ገደብ ቢያስቀምጥ የማያቋርጡ ዝውውሮችን ሊያስቀር ይችላል፡፡*
- *ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ከምክር ቤት ጀምሮ እስከ ባለበጀት መ/ቤቶች የበላይ አመራሮች በፕሮግራም በጀት ላይ ግንዛቤውን ሊፈጥርና በፕሮግራም አፈጻጸም ላይ የታዩ ክፍተቶችን ለመለየትና በታዩ ክፍተቶች ላይ የመፍትሔ ሐሳብ ለማምጣት ከላለበጀት መ/ቤቶች ጋር የመወያያ መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡*

132. **ሚኒስትር መ/ቤቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነትና እና ጠንካራ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ትስስር መኖሩን በተመለከተ፤**

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የፕሮግራም በጀት ወደ ክልል ለማውረድ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ እና ወደ ትግበራ አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮግራም በጀት አፈጻጸም የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት ችግሮቹን በመለየትና ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች ጋር በመወያየት የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስቀድሞ በመ/ቤቶች ላይ የፕሮግራም በጀት አሰራር ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት የመ/ቤቶችን ፍላጎት በመጠየቅ ስልጠና ሊሰጥና በፕሮግራም በጀት ላይ የተሻለ አሰራር እንዲመጣ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስትር መ/ቤቱ አሁን እየተሰራበት ያለውን ሶፍትዌር ከፕሮግራም በጀት አሰራር አንጻር ሊገመግምና ፕሮግራም በጀት ሊፈጽም የሚያስችል ሶፍትዌር እንዲኖር አስፈላጊውን ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

አባሪ 1

በናሙና በታዩ መ/ቤቶች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ

የማይጠናቀቁ ፕሮጀክቶች

ተራ ቁ.	መ/ቤቱ	የፕሮጀክቱ ስም	የተጀመረበት ቀን	የሚጠናቀቀብት ቀን	እስከ ሰኔ 30/08 ያለበት ደረጃ	ምርመራ
1	አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ	ዋናው ግቢ የዶርመተሪ ህንጻ ጥገና	ሐምሌ 2007	ህዳር 2008	77 በመቶ	
2		በሳይንስ ፋክልቲ የላይብረ ሪሥራ	በመጋት 19/07	በጥቅምት/08	64 በመቶ	
3		የሰሜን ካምፓስ የዶርንተሪ ጥገና	መስከረም /08	የካቲት /08	9.4 በመቶ	
4		ሜዲካል ፋክሊቲ ላይብረሪ	በታህሳስ 2001	2003	በ2008 ዓ.ም ማለቁ፣	
5		በጥቁር አንበሳ	በግንቦት 2005	ግንቦት 2006	59 በመቶ	
6		ጂ ፕላስ 10 ኮምፕሌክ ግንባታ በኮሜርስ እየተሰራ ያለው	በየካቲ/06	በየካቲት/08	77 በመቶ	
7		በዋና ካምፓስ የሚሰራው ኦርመንተሪ	ታህሳስ 07	በህዳር 09	38 በመቶ	
8		በጥቁር አንበሳ ኢመርጀንሲ ሜድሲን ዩኒት ግንባታ	ሚያዝያ 07	ሚያዝያ 08	33 በመቶ	
9		ሰላሌ ካምፓስ ሁለገብ ህንጻ ግባታና የዶርመንተሪ እድሳት	9/10/07	13/6/08	23 በመቶ	
	ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ				**እስከ ሰኔ 2007 ዓ.ም. ያለበት ደረጃ**	
1		የተማሪዎች መኖሪያ ሕንጻዎች ግንባታ/ግብርና ኮሌጅ/	መጋቢት 2003	ሚያዝያ 2005	70	
2		የተማሪዎች መኖሪያ ህንፃወች ግንባታ /ዋናው ካምፓስ/	ጥር 2004 ዓ.ም	የካቲት 2006	95	
3		የተማሪዎች መኖሪያ ህንፃወች ግንባታ /ዋናው ካምፓስ/	ነሐሴ 2004	መስከረም 2007	95	
4		የተማሪዎች መኖሪያ ወጪ ቆጣቢ/አዋዳ ካምፓስ/	ሰኔ 2004	መጋቢት 2006	መጠቃቀቂያ ላይ የደረሰ	

5		የተማሪዎች መኖሪያ ህንጻ ግንባታ/አዋዳ ካምፓስ/	ግንቦት 2005	ጥቅምት 2006	መጠናቀቂያ ላይ የደረሰ	
6		የተማሪዎች መኖሪያ ህንጻ ግንባታ/አዋዳ ካምፓስ/	ግንቦት 2005	ጥቅምት 2006	ላይ የተጠናቀቀ	
7		የቤተመጽሐፍት ግንባታ/ጤና ሳይንስ ኮሌጅ/	መጋቢት 2003 ዓ.ም	መስከረም 2008	81	
8		የመማሪያ ክፍል ህንጻ ግንባታ/ግብርና ኮሌጅ/	መጋቢት 2003	ሚያዝያ 2005	መጠናቀቂያ ላይ የደረሰ	
9		የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዮት ህንጻ/ዋናው ካምፓስ/	ጥር 2004	የካቲት 2006	92	
10		የግቢ አጥር ሥራ/በዋናው ካምፓስ/	ሰኔ 2004	ጥቅምት 2006	95	
11		የግቢ ውበት ሥራ/በዋናው ካምፓስ/	ሰኔ 2004	ጥቅምት 2006	95	
12		የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድ/በዋና ካምፓስ/	ሰኔ 2004	ጥቅምት 2006	95	
13		የመማሪያ ክፍል ህንጻ ግንባታ/አዋዳ ካምፓስ/	ታህሳስ 2005	ጥቅምት 2006	95	
14		የተማሪዎች መመገቢያ ህንጻ/በዋና ካምፓስ/	መጋቢት 2005	ሚያዝያ 2007	75	
15		የዕቃ ማከማቻ መጋዘን/በዋና ካምፓስ/	መጋቢት 2005	ሚያዝያ 2007	61.13	
					እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም. ያለበት ደረጃ	
16		የስፖርት ኮምፕሌክስ/ዋናው ካምፓስ/	ሰኔ 2004	ጥር 2006	59.19	
17		የአጥርና ግቢ ፕላን ሥራ/ጤና ሳይንስ ኮሌጅ/	ህዳር 2005	ጥቅምት 2006	62.34	
18		የቤተ መጽሐፍ ህንጻ ግንባታ/ዋናው ካምፓስ/	መጋቢት 2005	ሚያዝያ 2007	65.47	
19		የስታፍ መኖሪያ ሕንጻ ግንባታ/ጤና ሳይንስ ኮሌጅ/	ሰኔ 20005	ሰኔ 2008	59	
20		የምግብ ዕቃዎች ማከማቻ መጋዘን/በዋና ካምፓስ/	መጋቢት 2005	ሚያዝያ 2007	49.29	
21		የአስተደደር ማዕከል ህንጻ/በዋና ካምፓስ/	መጋቢት 2005	ሚያዝያ 2007	62.88	
22		ዋናው መጋዘን ህንፃ ግንባታ /በዋናው ካምፓስ/	መጋቢት 2005 ዓ.ም.	ሚያዝያ 2007	76.67	
23		ማዕከላዊ ጋራጅ ህንፃ ግንባታ /ዋናው ካመባስ/	መጋቢት 2005 ዓ.ም.	ሚያዝያ 2007	61.13	
24		የቤተ መጽሐፍት ህንፃ ግንባታ/ወንዶ ገነት/	መጋቢት 2005	ሚያዝያ 2007	53.45	
25		የተማሪዎች የመመገቢያ አዳራሽ ግንባታ /ወንዶ ገነት/	መጋቢት 2005	ሚያዝያ 2007	64.10	
26		የቤተ መጽሐፍት ህንፃ ግንባታ /አዋዳ ካምፓስ/	መጋቢት 2005	ሚያዝያ 2007	70	
27		የመሰብሰቢያ አዳራሽ/ጤና ሳይንስ ኮሌጅ/	መጋቢት 2005	ሚያዚያ 2007	50.37	
28		የሌክቸር ቴአትር/ጤና ሳይንስ ኮሌጅ/	ሰኔ 2005	ሰኔ 2008	59	

29		ሁለ ገብ ህንጻ/ግብርና ኮሌጅ/	ሰኔ 2005	መስከረም 2008	49.15	
30		የሲቪል ኢንጅነር ላቦራቶሪ/በዋናው ካምፓስ/	ሰኔ 2005	ሰኔ 2007	49.29	
31		የአይሲቲ ማዕከል ህንፃ/በዋናው ካምፓስ/	ሰኔ 2005	ሰኔ 2007	58.18	
32		የኤሌክትሪካል ላብራቶሪ ህንጻ/በዋናው ካምስ/	ሰኔ 2005	መስከረም 2008	46.85	
33		መካኒካል ላብራቶሪ ህንጻ/በዋናው ካምፓስ/	ሰኔ 2005	መስከረም 2008	47.61	
34		ኬሚካል ላብራቶሪ ህንጻ/በዋናው ካምፓስ/	ሰኔ 2005	መስከረም 2008	47.64	
	በዲላ ዩኒቨርስቲ				**እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም. ያለበት ደረጃ**	
1		የግቢ ውበት ግንባታ /7/ ኘሮጀክቶች	**6/5/07**	**6/9/07**	**30 በመቶ**	
2		ላይብረሪ /G+1/ 1 ብሎች ብሎክና ሳይት ወርክ	በ5/13/05	በ18/12/07	54 በመቶ	
3		የተማሪዎች ማደሪያ ዶርም	በሚያዚያ 06	በጥቅምት 2008	66 በመቶ	
4		የመማሪያ ብሎክ/ G+4/ 2 ብሎክ	5/13/2005	17/04/08	69 በመቶ	
5		የማዋለ ህፃናት ግንባታ /G+1/ ብሎክ	5/10/06	25/12/07	75 በመቶ	
6		የማማሪያ ብሎክ G+42 ብሎክ	9/11/07	9/12/08	11 በመቶ	
7		የቀለም ቅብ	11/07	22/1/08	56 በመቶ	
8		ሪፈራል ማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ	ጥቅምት 2006	ሰኔ 2008	25 በመቶ	
1	**አዳማ ዩኒቨርስቲ**					
2		ሁለገብ የመሰብሰቢያ አዳራሽ	ሰኔ/2005	ሰኔ/2008		
3		፤ማዕከላዊ አስተዳደርና የሴቶች ዶርሚተሪ	ሰኔ/ 2005	ሰኔ/2008	74.3 በመቶኛ	
4		ስታዲዩምና የስፖርት መጫወችያ ማዘወትሪያ	በ2005ሃምሌ	መስከረም 2007	87.8 በመቶኛ	
5		የላንድስኬፐ ዲዛይንማስተር ፕላን	ታህሳስ 2006	ህዳር 2007	99 በመቶኛ	
6		የዩሲቢ የፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ ፕላንት ስራና የኤሌክትሮ መካኒካል ዕቃዎች አቅርቦት ተከላ	መስከረም 2001	ሰኔ 2007	94.9 በመቶኛ	
7		ሁለገብ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ህንጻ	ሰኔ2005	በመጋቢት 2007	90.2 በመቶኛ	
8		የሱቆችና ተያያዝ ጉዳዮች	ሰኔ2005	በጥቅምት2007	99.5 በመቶኛ	
		/የአስፋልት ግንባታ	በ2006	በ2007 ጥር	98 በመቶኛ	
		ጥናትና ምርምር ፓርክ ግንባታ	በ2006	በ2009 ህዳር	55.61 በመቶኛ	
		የስፖርት አካዳሚ	በጥቅምት2006	በ2008 ሰኔ	97 በመቶኛ	

		የዩኒቨርስቲው የመግቢያ መውጫ በሮች፤የማዳረሻ መንገዶች የመሬት ማስተካከልና የግቢ ስራዎች	በ2007 በጥቅምት ወር	በሰኔ በ2007	እቅዱም5 ነበር በ2008 ተከናውኗል/5/	
	የውሃ፣ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር				**እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም. ያለበት ደረጃ**	
1		አርጆ ድዴሳ ግድብ ግንባታ	የካትት 2003	ሰኔ 2007	34.66 በመቶኛ	
2		አድአ-በቾ ግፌት መስኖ ፕሮጀክት 5000 ሄ/ር መሬት ዝግጅት/የሪቴንሽን ክፍያዎች/ፕሮጀክት	ሚያዚያ 2004	ሰኔ 2007	33.7 በመቶኛ	
3		የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ግንባታ ፕሮጀክት(EU/EIB የሚደገፍ)ፕሮጀክት	ጥር 2003	ሰኔ 2008	39.88 በመቶኛ	
4		የከሰም ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት	መጋቢት 1997 ዓ.ም.	ሰኔ 2008	24.99 %	
5		ተንዳሆ ህብረተሰቡ 1,055 ሄ/ር የመስኖ መሬት ፕሮጀክት	መጋቢት 1997 ዓ.ም.	ሰኔ 2008	3.97 %	
6		የከሰም ቦልሃሞ ስኳር መሬት ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት	ሰኔ 2002 ዓ.ም.	ታህሳስ 2008	5.95 %	
7		የተንዳሆ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት	መጋቢት 1997 ዓ.ም.	ታህሳስ 2007	12.389	
8		ተንዳሆ ህብረተሰቡ 10,029 ሄ/ር የመስኖ መሬት ዝግጅት ፕሮጀክት	መጋቢት 1997 ዓ.ም	ሰኔ 2007	21.36 %	
9		የተንዳሆ ስኳር መሬት ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን ሥራ እና የአንድ ድልድይ ግንባታና የአንድ ድልድይ ዲዛይን ፕሮጀክት	ሰኔ 2002 ዓ.ም.	ሰኔ 2008	3.51 %	
10		የዳቡስ ቅድመዝርዝርና ዝርዝር ጥናት	2007	2009	7 %	አፈጻጸማቸው በጣም ዝቅተኛ ነው
11		የባዮፌል ልማት በገጠራቱ ኢትዮጵያ ፕሮጀክት	2005	2010	19.07 %	አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ነው

12		የነዳጅ ጥራት ቁጥጥር ቋሚና ተንቀሳቃሽ ላቦራቶሪ ቁሳቁስ ግዢ የሚደገፍ)ፕሮጀክት	ግንቦት 2006	ህዳር 2008	27 በመቶኛ	
13		የመገጭ ግድብ ግንባታ	መጋቢት 2004	ነሐሴ 2009	20.4 በመቶኛ	አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ነው
14		አርጆ ዴዴሳ PHASE 2 ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት	ግንቦት 2006	ታህሳስ 2009	26.25 በመቶኛ	አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ነው
15		የመገጭ(ሰራባ)የተገነባ የመስኖ አውታር ፕሮጀክት	-	-	19.83	የ2008 በጀት ዓመት አፈጻጸም
16		የተገነባ የርብ የመስኖ አውታር	-	-	23.99 %	“
17		የተዘጋጁ ጥናትና ዲዛይን ሰነዶች አውታር			13.15 %	“

አባሪ 2

<u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች</u>

አዲት ተደራጊ መ/ቤት፡- <u>ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር</u>

ኦዲት አከባቢ፣ <u>የኘሮግራም በጀት አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ</u>

የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/	አስተያየት /Comment/
1.1 የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለበጀት ዓመቱ የታቀዱ ውጤቶችና ግቦች መሳካታቸውን ለመደበኛ እንዲሁም ለካፒታል ኘሮጀክቶች የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተል በኘሮግራም በጀት አፈጻጸም ማንዋል በተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ባለበጀት መ/ቤቶች የድርጊት መርሐ ግብራቸውንና የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡	
1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለበጀት መ/ቤቶች የታቀዱት ግቦች የደረሱበት ደረጀና አፈጻጸም ካስቀመጡት መርሃ ግብር አንጻር በየጊዜው ክትትል በማድረግ እና በተገኙ ልዩነቶች ላይ በወቅቱ ማሻሻያ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡	
1.3 ሚኒስትር መ/ቤቱ ወቅታዊነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ በድንገት ወይም በተወሰነ ጊዜ ክትትል ለማድረግ መርሃ ግብር ሊያዘጋጅና በመርሃግብሩ መሰረትም ጉብኝት እናቅኝት በማድረግ ሊከታተልና በወቅቱ ያሉትን ክንዋኔዎች ድክመትና ጥንካሬን በመለየት የእርምት	

የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/	አስተያየት /Comment/
እምርጃዎችን ሊወስድና ሊስተካከል የሚገባቸውን የመፍትሔ አቅጣጫዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡	
1.4 ባለበጀት መ/ቤቶች የታቀዱት ግቦች የደረሱበት ደረጀና አፈጻጸም ካስቀመጡት መርሃ ግብር አንጻር በየጊዜው ክትትል በማድረግ እና በተገኙ ልዩነቶች ላይ በወቅቱ ማሻሻያ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡	
1.5 ለበጀት ዓመቱ የታቀዱ ውጤቶችና ግቦች መሣካታቸውን ለመደበኛ እንዲሁም ለካፒታል ኘሮጀክቶች የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተል በየሩብ ዓመቱ የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል፡፡	
1.6 ሚኒስትር መ/ቤቱ የታለመ የውጤቶች ውጤታማነትና የኘሮግራሞች የግብ ስኬት በኘሮግራም በጀት ዘመን ከተጣለው የግብ ስኬት አንጻር በእያንዳንዱ የኘሮግራም በጀት ዓመት የተገኘው ዓመታዊ የግብ ስኬት ምን ያህል እንደሆነ መገምገም ይኖርበታል፡፡	
2.1 ሚኒስትር መ/ቤቱ የኘሮግራም በጀትን በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም.ጀምሮ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡	
2.2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኘሮግራም በጀትን ወደ ክልሎች ለማውረድ እንዲቻል በኘሮግራም በጀት ቅድመ ዝግጅትና አተገባበር ላይ ተከታታይ ሥልጠናና ድጋፍ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡	
2.3 ሚኒስትር መ/ቤቱ የፀደቀውን የበጀት ቀመር	

የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/	አስተያየት /Comment/
በመጠቀም እና የጸደቀውን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ መሠረት በማድረግ የገ/ኢ/ትብብር ሚኒስትር የሦስት ዓመት ተንከባላይ የበጀት ድጋፍ ግምት ለእያንዳንዱ ክልላዊ መንግሥትና የአስተዳደር ምክር ቤት በማዘጋጀት በየዓመቱ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡	
2.4 ባለበጀት መ/ቤቶች ዓመታዊ የሚያከናውኑት ፕሮግራም ዝርዝር ዕቅድ /የፊስካል ዕቅድ/ ሊያዘጋጁ እና በጊዜ ሰሌዳው ላይ ባለው ቀን/ጥር 15/ ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊልኩ ይገባል፡፡	
2.5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮግራም በጀት ዙሪያ ባዘጋጀው እስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ዓመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡	
2.6 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ አስፈጻሚ መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀቱን ለመፈፀም የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል አደረጃጀት እና ግብዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡	
2.7 የሚኒስትር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀት እና ውጤት ተኮር ዕቅድ ተመጋጋቢ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡	
2.8 በፕሮግራሞች ወይም በፕሮጀክቶች እና በመደበኛ ዋና ተግባራት መካከል የሚደረግ የበጀት ዝውውር በፋይናንስ አስተደደር አዋጅ እና በፋይናስን ደንብ እንዲሁም በፕሮግራም በጀት የበጀት ዝውውር	

የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/	አስተያየት /Comment/
አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ሊከናወን ይገባል፡፡	
2.9 መ/ቤቶች የተጨማሪ በጀት ጥያቄያቸውን በጽሑፍ አዘጋጅተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርቡ፣ እንዲሁም ከባለበጀት መ/ቤቶች የሚቀርበውን ጥያቄ ሃሳብ መሠረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊዘጋጅ፣ ሊጠናቀር እንዲሁም በምክር ቤት በሚቀርበው ድጋፍ መሠረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደ አዲስ ሊጸድቅ ይገባል፡፡	
2.10 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከማክሮ ኢኮኖሚ ፊስካል ማዕቀፍ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ጸደቀው በጀት ማሳወቅ ያለው የሥራ ሂደት መመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሊያከናውን ይገባል፡፡	
2.11 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በባለበጀት መ/ቤቶች የሚገነቡት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ማለቃቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡	
2.12 የባለበጀት መ/ቤቶች የድርጊት መርሃ-ግብራቸውን አዘጋጀተው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳው መሠረት ሊያቀርቡና በመርሐ ግብሩ መሠረት ሊተገብሩ ይገባቸዋል፡፡	
2.13 መ/ቤቶች ፕሮግራማቸውን ሲያስቀምጡ የሥርዓተ ፆታ በበጀት ውስጥ ጎልቶ እንዲታይና ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ ለብቻው እንዲታይ መደረግ አለበት፡፡	
3.1 ሚኒስትር መ/ቤቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት ያለው መሆኑን	

የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/	አስተያየት /Comment/
ማረጋገጥ፡፡	
3.1.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የባለበጀት መ/ቤቶች በኘሮግራም በጀት ዙሪያ በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፐ፣ በደብዳቤና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ ሊፈጥር ይገባል፡፡	
3.1.2 በዕቅድ እና በበጀት ዝግጅት እንዲሁም በበጀት አስተዳደር ያጋጠሙ ችግሮችና ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮች በመለየት ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር በጋራ እና አስፈላጊ ሲሆን በተናጠል ውይይት ለማካሄድ ሰነድ በማዘጋጀት ውይይት ሊያደርግ ይገባል፡፡	
3.1.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሁሉም የባለበጀት መ/ቤቶች የኘሮግራም በጀትን አፈፃፀምን በሚመለከተ ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡	
3.2 ሚኒስትር መ/ቤቱ ዘመናዊና ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡	
3.2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለጀት መ/ቤቶች የኘሮግራም በጀት አሰራርን እና የመረጃ ልውውጥ የተቀላጠፈ እንዲሆን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት ሊጠቀም ይገባል፡፡	
3.2.2 ሚኒስትር መ/ቤቱ የባለበጀት መ/ቤቶችን የኘሮግራም ሠነዶችንና መረጃዎችን ለይቶና አደራጅቶ ለብቻው ማስቀመጥ አለበት፡፡	

የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/	አስተያየት /Comment/
3.2.3 የበጀት ዝውውሮችና የተጨማሪ በጀቶች በሚኒስትር መ/ቤቱ በተዘጋጀው የወጪ በጀት የሂሣብ መመዝገቢያ ካርድ ሊመዘገቡና ወቅታዊ በማድረግ ሊያዙ ይገባል፡፡	